ስቲሮት

ከመቶ በላይ የመጽሀፍ ቅዱስ ግጭቶች ከመጠነኛ ማብራሪያ ጋር

የሕያ ኢብኑ ኑህ

© የጸሀፊው መብት በህግ የተጠበቀ ነው
All Rights Reserved

የመጀመሪያ ህትመት

ማውጫ

መግቢያ 10

ምስጋና 11

1. ይመጣ ዘንድ የተባለው? 14

2. የመጻጻጥ ብዛት 15

3. ስምዖን እንዴት አወቀ? 16

4. መጀመሪያ ያገኙት የት ነበር? 16

5. ሞታ ነበር ወይንስ ገና አልሞተችም? 17

6. አዟቸዋል ወይንስ አላዘዛቸውም? 18

7. የሀንስ ነው ብሎ አስቦ ነበርን? 19

8. የሀንስ ስለ እሱ ይናገር ነበርን? እየሱስ ከመጠመቁ በፊት መጥምቁ የሀንስ ስለ እሱ ይናገር ነበርን? 20

9. ካጠመቀው በኋላስ ያውቀው ነበር? 21

10. እውነት ነው ወይንስ አይደለም? 22

11. የዛውን ቀን ነው ያጸዳው ወይንስ አይደለም? 22

12. ወዲያውኑ ነው የደረቀችው ወይንስ ቆይታ? 24

13. እየሱስን ስሞታል ወይንስ አልሳመውም? 24

14. ስለጴጥሮስ ክህደት እየሱስ በትክክል ምንድን ነበር ያለው? ስለጴጥሮስ ክህደት እየሱስ በትክክል ምንድን ነበር ያለው? 25

15. እራሱ ወይንስ ሌላ ሰው? 26
16. ከመቀደዱ በፊት ነው ወይንስ በኋላ? 27
17. ነበር ወይንስ አልነበረም? 28
18. እግዚአብሄር ወይስ ሰይጣን? 29
19. የእስራኤል ተዋጊዎች ብዛት 30
20. የዳዊት ተዋጊዎች ብዛት 31
21. የስንት አመት ረሀብ? 32
22. የአካዝያስ እድሜ 33
23. የዮአኪን ንግስና 34
24. ዮአኪን በእየሩሳሌም ለምን ያህል ጊዜ ነግሷል? 35
25. ዮዳዊት ሀያላን አለቃ በአንድ ጊዜ ምን ያህል ሰዎችን ገደለ? 36
26. ዳዊትና የእግዚአብሄር ታቦት 37
27. የፍጡራን ብዛት በኖህ መርከብ ውስጥ 37
28. ምርኮኛ ፈረሶች 38
29. ሰለሞን ምን ያህል የፈረስ ጋጦች ነበሩት? 38
30. የእስራኤል ንጉስ ባአስ 39
31. ለሰለሞን ቤተ-መቅደስ ስራ የተሳተፉ ሰዎች ምን ያህል ናቸው? . 40
32. ምን ያህል የባዶስ መስፈሪያ ይይዝ ነበር? 41
33. የፈሐት ሞዐብ ልጆች ብዛት 41
34. የዛቱ ልጆች ምን ያህል ናቸው? 42

35. የአዝጋድ ልጆች ስንት ናቸው? 42
36. የአዲን ልጆች ምን ያህል ናቸው? 43
37. የሀሱም ልጆች ምን ያህል ናቸው? 43
38. የቤቴልና የጋይ ሰዎች ምን ያህል ናቸው? 43
39. የጉባኤው ብዛት 44
40. ምን ያህል መዘምራን ነበሩ? 44
41. የንጉስ አብያ እናት ስም ማን ነበር? 45
42. እያሱና እስራኤላውያን በርግጥ እየሩሳሌምን ተቆጣጥረዋልን? .. 46
43. የማርያም እጮኛ የነበረው ዮሴፍ አባቱ ማን ነበር? 46
44. እየሱስ ከየትኛው የዳዊት ዘር የተገኘ ነው? 47
45. የሶላትያል አባት ማን ነው? 48
46. የየትኛው የዘሩባቤል ልጅ ነው የእየሱስ ቅድመ አያት? 48
47. የዖዝያን አባት ማነው? 49
48. የኢኮንያ አባት ማነው? 50
49. ከዳዊት እስከ ባቢሎን ምርኮ ምን ያህል ትውልድ ነው? 50
50. የሳላ አባት ማነው? 51
51. ሁለቱም ወይንስ አንዱ? 52
52. እየሱስን በሰቀሉት ጊዜ ስንት ሰዐት ነበር? 53
53. እየሱስ በተሰቀለበት ቀን ወደ መንግስተ ሰማያት ገብቷልን? 53
54. አብረው የነበሩ ሰዎች 54

55. ወድቀዋል ወይንስ አልወደቁም? 55

56. የ«ራዕዩ» ድምጽ ጳውሎስ ምን መስራት እንዳለበት ነግሮታልን? 56

57. በመቅሰፍት የሞተው ሰው ብዛት ስንት ነው? 57

58. ወደ ግብጽ የገቡት የያዕቆብ ቤተሰቦች ምን ያህል ናቸው? 59

59. ይሁዳ እየሱስን በመክዳቱ ያገኘውን ገንዘብ ምን አደረገው? 59

60. ይሁዳ እንዴት ሞተ? 60

61. የደም መሬት የተባለው ለምንድን ነው? 61

62. ማን ለማን ቤዛ ነው? 62

63. የሙሴ ህግ ጠቃሚ ነውን? 63

64. የሙሴ ህግ ተሸሯል ወይንስ አልተሻረም? 64

65. በክሱ ጽህፈት ላይ የተጻፈው ቃል ምንድን ነበር? 65

66. ሄሮድስ መጥምቁ የሀንስን መግደል ይፈልግ ነበርን? 65

67. አስረኛው ማነው? 66

68. የተከተለው ሰው ማነው? 68

69. እየሱስ የተሰቀለው ከፋሲካ ማዘጋጀት በፊት ነው ወይንስ በኋላ? 69

70. ስቅለቱ እንዲቀርለት እየሱስ ለአባቱ ጸልዮ ነበርን? 70

71. ጊዜው ምን ያክል ነው? 71

72. በጸሎቱ ምን አለ? 74

73. መቶ አለቃው እየሱስ በሞተ ጊዜ ምንድን ነበር ያለው? 75

ስቲሮት

74. እንደ ወንጌላት አገላለጽ እየሱስ ከመሞቱ በፊት መጨረሻ ያለው ቃል ምንድን ነው? 75

75. መቶ አለቃው እራሱ ነው የመጣው ወይንስ ሰዎችን ነው የላከው? 76

76. አዳም የተከለከለውን ዛፍ የበላ ቀን ሙቷል ወይንስ አልሞተም?77

77. የሰው ልጅ የእድሜ ገደብ ስንት ነው? 78

78. ከእየሱስ ውጭ ወደ ሰማይ የወጣ አለ? 79

79. በስርዐት ተከፍኗል ወይንስ አልተከፈነም? 79

80. ሴቶቹስ ሽቶውን መቼ ነው የገዙት?..... 80

81. ሴቶቹ ወደ መቃብሩ የመጡት ለምንድን ነበር? 81

82. ሴቶቹ ወደ መቃብር የመጡት መቼ ነው? 82

83. ወደ መቃብሩ ሲመጡ ስንት ነበሩ? 83

84. ቋጥኙ የት ነበር? 84

85. ለሴቶቹ በእየሱስ አካል ዙርያ የነገራቸው አካል ነበር?..... 85

86. የትና በምን ሁኔታ? 87

87. እየሱስ ለደቀመዛሙርቱ ያስተላለፈው መልዕክት ምንድን ነበር? 88

88. የምድያም ነጋዴዎች ዮሴፍን ለማን ነበር የሸጡት?..... 89

89. ዮሴፍን ወደ ግብጽ ያመጣው ማን ነው? 89

90. አምላክ ይጸጸታል ወይንስ አይጸጸትም? 90

91. የትኛውን ውሀ ቀየሩት? 92

92. ጎልያድን የገደለው ማን ነው?..... 92

93. ሳዖልን የገደለው ማን ነው?..... 93

94. ሁሉም የሰው ልጅ ሀጥያት ይሰራል ወይስ አይሰራም? 94

95. እያንዳንዱ የማንን ሸክም ይሸከም?..... 95

96. እየሱስ ከትንሳኤ በኋላ ለስንት ደቀመዛሙርት ነው የታያቸው? 96

97. እየሱስ ከተጠመቀ በኋላ በሶስተኛው ቀን የት ነበር? 97

98. ሄሮድስ እየሱስ በልጅነቱ ሳለ ነው የሞተው ወይንስ ከዚያ በኃላ ነው?..... 98

99. እየሱስ በውሀ ላይ በሚራመድበት ወቅት ደቀመዛሙርት ምንድን ነበር የመለሱት? 99

100. ለእግዚአብሄር ፍጥረቱ መልካም ነበር ወይንስ አልነበረም? 100

101. እግዚአብሄር ቤተ መቅደስ ውስጥ ስሙ ለዘላለም ይኖራልን ወይንስ አይኖርም?..... 101

102. እግዚአብሄር ቁጣው ዘላለማዊ ነው ወይንስ ጊዜያዊ? 102

103. በእውኑ ምንም ጻድቅ የለምን ወይንስ አለ?..... 103

104. እግዚአብሄር ይታያል ወይንስ አይታይም?..... 104

105. ከእርግዝና በፊት ነው ወይንስ በኋላ?..... 105

106. መላእኩ ብስራቱን የተናገረውስ ለማን ነበር?..... 106

107. ከተወለደ በኋላስ ስሙ ማን ይባላል?..... 107

108. ከሰማይ የመጣው ድምጽ የተናገረው ለእየሱስ ነበር ወይንስ ለተሰበሰበው ህዘብ?..... 108

109. እየሱስ ወደ ቅፍርንሆም የሄደው ብቻውን ነው ወይንስ ከደቀመዛሙርቱ ጋር..... 109

110. ጴጥሮስ ወንጌልን የሰበከው ለአይሁዳውያን ብቻ ነው ወይንስ ለአህዛብም ጭምር? 110

111. እየሱስ የጴጥሮስን አማት የፈወሳት ለምጻሙን ከፈወሰ በኋላ ነው ወይንስ በፊት?..... 111

112. እየሱስ ወላጅን ስለማክበር..... 112

113. እየሱስና «ስድብ»..... 113

114. መልካም ስራ በሰው ፊት ነው ወይንስ በድብቅ ነው መሆን ያለበት? 114

115. ሴት ልጅ መውለድ መባረክ ነው ወይንስ መርከስ?..... 115

116. ቃየል ከእግዚአብሄር ፊት ተሰውሯልን?..... 116

117. የአብርሀም አባት ታራም አብርሀምን ሲወልድ እድሜው ስንት ነበር? 117

118. ከባቢሎን ግንብ ግንባታ በፊት ብዙ ቋንቋዎች ነበሩ ወይንስ አልነበሩም? 118

119. እግዚአብሄር ስለ መስዋዕት አዟል ወይንስ አላዘዘም?..... 118

መግቢያ

ይህችን አነስተኛ ይዘት ያላት መፅሀፍ ለመፃፍ ስነሳ በዋናነት ትኩረት አድርጌው የነበረው አጀንዳ ስለመፅሀፉ ተዓማኒ አለመሆን ለመግለጽ የማቀርበው ማሳያ ምንድን ነው? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ ነበር። እንደ ሙስሊም በመፅሀፍ ቅዱስ የአምላክ ቃልነት የማላምንበት ዋነኛ ምክንያት መፅሀፉ "ተበርዟል" ብየ ስለማምን ነው። ይህን ሀሳብ ለአንድ ክርስቲያን ስመልስለት ወዲያው የሚያነሳልኝ የአጸፋ ጥያቄ "ለመበረዙ ማስረጃህ ምንድን ነው?" የሚለው ነው። ለመበረዙ ብዙ ማስረጃዎች ያሉኝ ሲሆን ከነዛ መካከል አንዱ መፅሀፍ ቅዱስ እርስበርሱ ይጋጫል የሚለው ሀሳብ ነው፤ መለኮታዊ መፅሀፍ ደግሞ ከስህተት የጠራ እንደመሆኑ መጠን እነኝህ ግጭቶች ሲገኙበት መለኮታዊ መመሪያነቱ ጥያቄ ውስጥ ይገባል።

ታዲያ ይህች መፅሀፍም ለተጠየቅኩት የአፀፋ ጥያቄ ያስቀመጥኳት ምላሼ ብቻ ናት፤ የማምንበትን ለማስተማሪያ ካገለገለ ብየ አካፍያችኃለሁ። ህሊና ጥሩ ዳኛ ነውና መርምራችሁ ወስኑ.!

መፅሀፉን አስመልክቶ የሚመጡ አሉታዊም ሆነ አወንታዊ አስተያየቶችን ለመቀበል በሬ ክፍት ነው። በፌስቡክና ቴሌግራም አድራሻየ ያገኙኛል።

የሕያ ኢብኑ ኑህ

ምስጋና

በመጀመሪያ መፅሀፉን የምጽፈበትን ሀይልና መረዳት የሰጠኝን የአለማቱ ጌታ አላህ (ሱ.ወ) አመሠግነዋለሁ። በመቀጠል መፅሀፉን በማሳተም ረገድ የበኩላቸውን ጥረት ላደረጋቸውልኝ ወዳጆቼ ሁሉ ምስጋናየ ከልብ ነው። በልጅነት ህይወቴ ወንጌልን ልትሰብኩኝ ቀርባቸሁኝ ወንጌልን እንዳጠናና እምነቴንም እንዳውቅ ያገዛቸሁኝን ወንጌላውያንም ምንም እንኳ የፈለጋቸሁትን አይነት ሰው ባልሆንም መሆን የሚኖርብኝን አይነት ሰው እንድሆን አግዛቸሁኛልና አመሰግናለሁ።

ማስታወሻነቱ

ይህንን መፅሀፍ በንጹህ ልቦናህና እውነትን ለማወቅ አስበህ ለምታነበው ለአንተ

ስቲሮት

ስቲሮት ማለት የእብራይስጥኛ /סְתִירָה/ ቃል ሲሆን ትርጉሙ "ግጭቶች" ወይንም በእንግሊዝኛው Contradictions የሚል ፍች አለው።

1. **ይመጣ ዘንድ የተባለው?**

"ልትቀበሉትስ ብትወዱ፥ ይመጣ ዘንድ ያለው ኤልያስ ይህ ነው። " (የማቴዎስ ወንጌል 11: 14)

በተመሳሳይ
« ደቀ መዛሙርቱም፦ እንግዲህ ጻፎች፦ ኤልያስ አስቀድሞ ሊመጣ ይገባዋል ስለ ምን ይላሉ? ብለው ጠየቁት። ኢየሱስም መልሶ፦ ኤልያስማ አስቀድሞ ይመጣል ሁሉንም ያቀናል፤ ነገር ግን እላችኋለሁ፥ ኤልያስ ከዚህ በፊት መጣ፤ የወደዱትንም ሁሉ አደረጉበት እንጂ አላወቁትም፤ እንዲሁም ደግሞ የሰው ልጅ ከእነርሱ መከራ ይቀበል ዘንድ አለው አላቸው። በዚያን ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ስለ መጥምቁ ስለ ዮሐንስ እንደ ነገራቸው አስተዋሉ።» ማቴዎስ 17፡10-13

እነኝህ አንቀጾች የሚገልጹት ይመጣ ዘንድ የተባለው **ኤልያስ** እንደሆነ ነው፡፡ ነገር ግን በሌላ አንቀጽ

"አይሁድም፦ አንተ ማን ነህ? ብለው ይጠይቁት ዘንድ ከኢየሩሳሌም ካህናትንና ሌዋውያንን በላኩበት ጊዜ፥ የዮሐንስ ምስክርነት ይህ ነው።መሰከረም አልካደምም፤ እኔ ክርስቶስ አይደለሁም ብሎ መሰከረ። እንኪያስ ማን ነህ? ኤልያስ ነህን? ብለው ጠየቁት። + ነቢዩ ነህን? አይደለሁም ብሎ መለሰ።» ዮሀንስ 1፡19-21

ጥያቄው፦ ይጠበቅ የነበረው ኤልያስ - መጥምቁ ዮሀንስ ነበረ ወይንስ አልነበረም?

2. <u>የመጓጓዣ ብዛት</u>

«ውርንጫውንም ወደ ኢየሱስ አመጡት፥ ልብሳቸውንም በላዩ ጣሉ፥ ተቀመጠበትም።»

ማርቆስ ፲፡7

በተጨማሪም "ወደ ኢየሱስም አመጡት፥ **በውርንጫውም** ላይ ልብሳቸውን ጭነው ኢየሱስን አስቀመጡት።" (የሉቃስ ወንጌል 19: 35)

በነዚህ አንቀጽ መሰረት እየሱስ ወደ እየሩሳሌም የሄደው **በአንድ ውርንጭላ** ብቻ ነው፤ አባባሉ የሚጠቁመው ነጠላ ገለጻን ነውና።

ነገር ግን በሌላ ቦታ ላይ

"ለጽዮን ልጅ። እነሆ፥ ንጉሥሽ የዋህ ሆኖ **በአህያ ላይና በአህያይቱ ግልገል በውርንጫይቱ ላይ** ተቀምጦ ወደ አንቺ ይመጣል በሉአት ተብሎ በነቢይ የተነገረው ይፈጸም ዘንድ ይህ ሆነ። ደቀ መዛሙርቱም ሄደው ኢየሱስ እንዳዘዛቸው አደረጉ፥ አህያይቱንና ውርንጫዋንም አመጡለት፥ ልብሳቸውንም በእነርሱ ላይ ጫኑ፥ ተቀመጠባቸውም።" የማቴዎስ ወንጌል 21፥4-7

በዚህኛው አንቀጽ ደግሞ መጓጓዣዎቹ አህያና ውርንጭላ እንደሆኑ ተገልጸዋል።

ጥያቄው፡- እየሱስ በስንት መጓጓዣ ነው ወደ እየሩሳሌም የመጣው? የሚል ነው።

3. ስምዖን እንዴት አወቀ?

«ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አለው፦ የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ፥ **በሰማያት ያለው አባቴ እንጂ** ሥጋና ደም ይህን አልገለጠልህምና ብፁዕ ነህ።» ማቴወስ 16፡17

ይህ አንቀጽ እንደሚ-ገልጸው ስምኣን ክርስቶስን ያወቀው ተገልጦለት ነው፡፡ በሌላ አንቀጽ ግን እንዲህ ይላል

«ከዮሐንስ ዘንድ ሰምተው ከተከተሉት ከሁለቱ አንዱ የስምዖን ጴጥሮስ ወንድም እንድርያስ ነበረ።እርሱ አስቀድሞ የራሱን ወንድም ስምዖንን አገኘውና፦ **መሢሕን አግኝተናል አለው**፤ ትርጓሜውም ክርስቶስ ማለት ነው።ወደ ኢየሱስም አመጣው። ኢየሱስም ተመልከቶ፦ አንተ የዮና ልጅ ስምዖን ነህ፤ አንተ ኬፋ ትባላለህ አለው፤ ትርጓሜው ጴጥሮስ ማለት ነው። ›

ዮሀንስ 1፡41-43

ይህኛው አንቀጽ የሚነግረን ደግሞ ክርስቶስ መሆኑን ለስምኣን የነገረው ወንድሙ እንድርያስ እንደሆነ ነው፡፡

ጥያቄው፦ ስለ ክርስቶስ የዮና ልጅ ያወቀው በራዕይ ነው ወይንስ ከወንድሙ ሰምቶ ነው? የሚል ነው፡፡

4. መጀመሪያ ያገኙት የት ነበር?

ስምኣንና እንድርያስ እየሱስን መጀመሪያ ያገኙት የት ነበር?

«እርሱ አስቀድሞ የራሱን ወንድም ስምዖንን አገኘውና፦ መሢሕን አግኝተናል አለው፤ ትርጓሜውም ክርስቶስ ማለት ነው» ዮሀንስ 1፡42

ይህ የሆነው ደግሞ ከላይ ባሉት አንቀጾች እንደሚገልጸው **በዮርዳኖስ ወንዝ** ነው።።ይህም ወደ ገሊላ ከመሄዱ በፊት ማለት ነው።።ቀጣዩ አንቀጽ እንዲህ ይላል።።

«በነገው ኢየሱስ ወደ ገሊላ ሊወጣ ወደደ፥ ፊልጶስንም አገኘና፦ ተከተለኝ አለው።» ዮሀንስ 1፡44

ነገር ግን በሌላ ቦታ እንዲህ ይላል

«በገሊላ ባሕር አጠገብ ሲመላለስም ሁለት ወንድማማች ጴጥሮስ የሚሉትን ስምዖንን ወንድሙንም እንድርያስን መረባቸውን ወደ ባሕር ሲጥሉ አየ፥ ዓሣ አጥማጆች ነበሩና። እርሱም፦ በኋላዬ ኑና ሰዎችን አጥማጆች እንድትሆኑ አደርጋችኋለሁ አላቸው።ወዲያውም መረባቸውን ትተው ተከተሉት።»ማቴወስ 4፡18-20

ጥያቄው: ስምዖንና አንድሪያስ እየሱስን መጀመሪያ ያገኙት የት ነበር?

5. <u>ሞታ ነበር ወይንስ ገና አልሞተችም?</u>

<u>መኮንኑ ወደ እየሱስ በመጣ ጊዜ የመኮንኑ ልጅ ሞታ ነበር ወይንስ ገና አልሞተችም?</u>

«ይህንም ሲነግራቸው፥ አንድ መኰንን መጥቶ፦ **ልጄ አሁን ሞተች**፤ ነገር ግን መጥተህ እጅህን ጫንባት፥ በሕይወትም ትኖራለች እያለ ሰገደለት።» ማቴዎስ 9፡18

ይህ አንቀጽ በግልጽ እንደሚነግረን የመኮንኑ ልጅ መሞቷን ነው፡፡ ነገር ግን ሌላ ቦታ ላይ ይህንን እናገኛለን፡፡

«ታናሽቱ ልጄ **ልትሞት ቀርባለችና** እንድትድንና በሕይወት እንድትኖር መጥተህ እጅህን ጫንባት ብሎ አጥብቆ ለመነው።» ማርቆስ 5፡23

ጥያቄው: ልጅቱ ሞታለች ወይንስ ገና አልሞተችም ነበር?

6. <u>አዟቸዋል ወይንስ አላዘዛቸውም?</u>

<u>እየሱስ ለመንገድ በትር እንዲይዙ አዟቸዋል ወይንስ አላዘዛቸውም?</u>

«ለመንገድም **ከበትር በቀር** እንጀራም ቢሆን ከረጢትም ቢሆን መሐለቅም በመቀነታቸው ቢሆን እንዳይዙ አዘዛቸው።» ማርቆስ 6፡8

በዚህ አንቀጽ ከሌላው ተለይቶ በትር ይይዙ ዘንድ እንደተፈቀደላቸው ይገልጻል፡፡ ነገር ግን በሌላ ቦታ ተቃራኒ ነገር እናገኛለን፡፡

"እንዲህም አላቸው፦ **በትርም ቢሆን**፥ ከረጢትም ቢሆን፥ እንጀራም ቢሆን፥ ብርም ቢሆን ለመንገድ ምንም አትያዙ፥ ሁለት እጅ ጠባብም አይሁንላችሁ።» ሉቃስ 9፡3

ተጨማሪ ማቴዎስ 10:9 መመልከት ይቻላል

ጥያቄው: እየሱስ በትር ይይዙ ዘንድ አዟቸዋል ወይንስ አላዘዛቸውም?

7. <u>የሀንስ ነው ብሎ አስቦ ነበርን?</u>

<u>ሄሮድስ "እየሱስ" መጥመቁ የሀንስ ነው ብሎ አስቦ ነበርን?</u>

«ሄሮድስ ግን ሰምቶ፦ እኔ ራሱን ያስቈረጥሁት **የሐንስ ይህ ነው** እርሱ ከሙታን ተነሥቶአል አለ። » ማርቆስ 6:16

በተመሳሳይ ማቴወስ ላይም ይህንን እናገኛለን::

«ለሎሌዎቹም፦ ይህ **መጥምቁ የሐንስ ነው**፤ እርሱ ከሙታን ተነሥቶአል፥ ስለዚህም ኃይል በእርሱ ይደረጋል አለ።»ማቴዎስ 14:2

ይህ አንቀጽ እንደሚነግረን ሄሮድስ ስለ እየሱስ ያስብ የነበረው መጥምቁ የሀንስ ከሙታን ተነስቶ እንደመጣ ነበር::

በሌላ አንቀጽ ግን ይህንን እናገኛለን

«ሄሮድስም፦ **የሐንስንስ እኔ ራሱን አስቈረጥሁት**፤ ይህ እንዲህ ያለ ነገር የምሰማበት ማን ነው? አለ። ሊያየውም ይሻ ነበር።» ሉቃስ 9:9

ጥያቄው እውን ሄሮድስ እየሱስ መጥምቁ ዮሀንስ ነበር ብሎ ነው የሚያስበው ወይንስ ሌላ ሰው እንደሆነ ነበር የሚያስበው?

8. ዮሀንስ ስለ እሱ ይናገር ነበርን?

እየሱስ ከመጠመቁ በፊት መጥምቁ ዮሀንስ ስለ እሱ ይናገር ነበርን?

«ያን ጊዜ ኢየሱስ በዮሐንስ ሊጠመቅ ከገሊላ ወደ ዮርዳኖስ ዮሐንስ ግን፦ እኔ በአንተ ልጠመቅ ያስፈልገኛል አንተም ወደ እኔ ትመጣለህን? ብሎ ይከለክለው ነበር።» ማቴዎስ 3፡13-14

በዚህ አንቀጽ ዮሀንስ እየሱስ በሚገባ እንደሚያውቀው ያሳያል።።

በሌላ በኩል ግን እንዲህ ይላል

<< **እኔም አላውቀውም ነበር፥** ዳሩ ግን በውኃ አጠምቅ ዘንድ የላከኝ እርሱ፦ መንፈስ ሲወርድበትና ሲኖርበት የምታየው፥ በመንፈስ ቅዱስ የሚያጠምቅ እርሱ ነው አለኝ።» ዮሀንስ ፡33

ጥያቄው: መጥመቁ ዮሀንስ እየሱስን ከማጥመቁ በፊት ያውቀው ነበር ወይንስ አያውቀውም?

9. ካጠመቀው በኋላስ ያውቀው ነበር?

መጥመቁ ዮሀንስ እየሱስን ካጠመቀው በኋላስ ያውቀው ነበር?

"ዮሐንስም እንዲህ ብሎ መሰከረ፦ መንፈስ ከሰማይ እንደ ርግብ ሆኖ ሲወርድ አየሁ፤ በእርሱ ላይም እኔም አላውቀውም ነበር፥ ዳሩ ግን በውኃ አጠምቅ ዘንድ የላከኝ እርሱ፦ መንፈስ ሲወርድበትና ሲኖርበት የምታየው፥ በመንፈስ ቅዱስ የሚያጠምቅ እርሱ ነው አለኝ።›ዮሀንስ ፡32-33›

በዚህ አንቀጽ እንደምናየው መጥምቁ ዮሀንስ እየሱስን ካጠመቀው በኋላ የሚመጣውና በመንፈስ ቅዱስ የሚያጠምቀው እየሱስ እንደሆነ ጠንቅቆ አውቋል።

«ዮሐንስም በወህኒ ሳለ የክርስቶስን ሥራ ሰምቶ ከደቀ መዛሙርቱ ሁለት ላከና የሚመጣው አንተ ነህን? ወይስ ሌላ እንጠብቅ? አለው።» ማቴወስ ፲፤2-3

በዚህ አንቀጽ ደግሞ ዮሀንስ በመጨረሻ እስር ቤት ሆኖ በነበረበት ወቅት እየሱስ የሚመጣው ይሁን አይሁን እንደማያውቅ ይነግረናል። ደቀመዝሙር ልኮ ሳይቀር እሱ መሆኑንና አለመሆኑን ይጠይቃል።

ጥያቄው፦ መጥምቁ ዮሀንስ እየሱስ ማን እንደነበር በርግጥኝነት ያውቅ ነበር ወይንስ አያውቅም?

10. እውነት ነው ወይንስ አይደለም?

እኔ ስለ እኔ ስለ ራሴ ብመሰክር **ምስክሬ እውነት አይደለም**፤» ዮሀንስ 5፡31

ከዚህ በተቃራኒው ደግሞ እዛው የሀንስ ወንጌል ውስጥ የተገላቢጦሽ እንዲህ ይለናል

ኢየሱስ መለሰ አላቸውም፦ እኔ ስለ ራሴ ምንም እንኳ ብመሰክር ከወዴት እንደመጣሁ ወዴትም እንድሄድ አውቃለሁና **ምስክርነቴ እውነት ነው**፤ እናንተ ግን ከወዴት እንደ መጣሁ ወዴትም እንድሄድ አታውቁም።» ዮሀንስ 8፡14

ጥያቄው ፡እየሱስ ስለራሱ ቢመሰክር ምስክርነቱ እውነት ነው ወይንስ አይደለም?

11. የዛውን ቀን ነው ያጸዳው ወይንስ አይደለም?

"ኢየሱስም ወደ መቅደስ ገባና በመቅደስ የሚሸጡትንና የሚገዙትን ሁሉ አወጣ፥ የገንዘብ ለዋጮችንም ገበታዎች የርግብ ሻጮችንም ወንበሮች ገለበጠና፦ቤቴ የጸሎት ቤት ትባላለች ተብሎ ተጽፎአል፥ እናንተ ግን የወንበዶች ዋሻ አደረጋችኋት በመቅደስም ዕውሮችና አንካሶች ወደ እርሱ ቀረቡና ነገር ግን የካህናት አለቆችና ጻፎች ያደረገውን ድንቃ ድንቅ በመቅደስም፦ ሆሣዕና ለዳዊት ልጅ እያሉ የሚጮኹትን ልጆች ባዩ ጊዜ፥ እነዚህ የሚሉትን አትሰማምን? አሉት። ኢየሱስም፦ እሰማለሁ፤ ከሕፃናትና ከሚጠቡት አፍ ምስጋናን ለራስህ አዘጋጀህ የሚለውን ቃል ከቶ አላነበባችሁምን?

ትቶአቸውም ከከተማ ወደ ቢታንያ ወጣ በዚያም አደረ። በማለዳም ወደ ከተማ ሲመለስ ተራበ።» ማቴዎስ 21፡12-18

ይህ አንቀጽ እንደሚነግረን እየሱስ መቅደሱን ያጸዳው ወደ ቢታንያ ከመሄዱ በፊት የዛውን ቀን ሲሆን በተቃራኒው ደግሞ ማርቆስ እንዲህ ይለናል፡፡

"ኢየሱስም ወደ ኢየሩሳሌም ወደ መቅደስ ገባ፤ ዘወር ብሎም ሁሉን ከተመለከተ በኋላ፥ ጊዜው መሽቶ ስለ ነበረ ከአሥራ ሁለቱ ጋር ወደ ቢታንያ ወጣ።በማግሥቱም ከቢታንያ ሲወጡ ተራበ።ቅጠልም ያላት በለስ ከሩቅ አይቶ ምናልባት አንዳች ይገኝባት እንደ ሆነ ብሎ መጣ፥ ነገር ግን የበለስ ወራት አልነበረምና መጥቶ ከቅጠል በቀር ምንም መልሶም፦ ከአሁን ጀምሮ ለዘላለም ማንም ከአንቺ ፍሬ አይብላ አላት። ደቀ መዛሙርቱም ወደ ኢየሩሳሌምም መጡ። ወደ መቅደስም ገብቶ በመቅደስ የሚሸጡትንና የሚገዙትን ያወጣ ጀመር፥ የገንዘብ ለዋጮችንም ገበታዎች የርግብ ሻጮዎችንም ወንበሮች ዕቃም ተሸክሞ ማንም በመቅደስ ሊያልፍ አስተማራቸውም፦ ቤቴ ለአሕዛብ ሁሉ የጸሎት ቤት ትባላለች ተብሎ የተጻፈ አይደለምን? እናንተ ግን የወንበዶች ዋሻ አደረጋችኋት አላቸው።ማርቆስ 11፥11-17

ጥያቄው፦ እየሱስ ቤተ መቅደሱን ያጸዳው ወደ ቢታንያ ከመሄዱ በፊት የዛውን ቀን ነው ወይንስ ከቢታንያ ሲመለስ በበነጋታው ነው?

12. ወዲያውኑ ነው የደረቀችው ወይንስ ቆይታ?

በመንገድም አጠገብ በለስ አይቶ ወደ እርስዋ መጣ፤ ከቅጠልም ብቻ በቀር ምንም አላገኘባትምና፦ ለዘላለሙ ፍሬ አይገኝብሽ አላት። በለሲቱም **ያንጊዜውን ደረቀች**።»
ማቴወስ 21፡19

ይህ አንቀጽ የሚነግረን በለሷ ዛፍ የደረቀችው ያን ጊዜ ማለትም በረገማት ቅጽበት ነው።።

ነገር ግን ሌላ ቦታ ላይ እንዲህ ይላል።።

«**ማለዳም ሲያልፉ** በለሲቱን ከሥርዋ ደርቃ አዩአት። ጴጥሮስም ትዝ ብሎት፦ መምህር ሆይ፥ እነሆ፥ የረገምሃት በለስ ደርቃለች አለው።» ማርቆስ 11፡20-21

ማርቆስ የሚነግረን መድረቋን ያወቁት ማለዳ ነው።።

ጥያቄው: በለሷ የደረቀችው የዛኔ ነውን ወይስ ቆይታ ነው?

13. እየሱስን ስሞታል ወይንስ አልሳመውም?

«አሳልፎ የሚሰጠውም፦ የምስመው እርሱ ነው፤ ያዙት ብሎ ምልክት ሰጥቶአቸው ወዲያውም ወደ ኢየሱስ ቀረበና፦ መምህር ሆይ፥ ሰላም ለአንተ ይሁን ብሎ **ሳመው**።ኢየሱስም፦ ወዳጄ ሆይ፥ ለምን ነገር መጣህ? አለው። በዚያን ጊዜ ቀረቡ እጃቸውንም በኢየሱስ ላይ ጫኑበት ያዙት።»
ማቴወስ 26፡48-50

ይህ አንቀጽ በግልጽ ይሁዳ እየሱስን እንደሳመው ይነግረናል። በሌላ ቦታ ግን እንዲህ ይላል።

«ኢየሱስም የሚመጣበትን ሁሉ አውቆ ወጣና፦ ማንን ትፈልጋላችሁ የናዝሬቱን ኢየሱስን ብለው መለሱለት። ኢየሱስ፦ እኔ ነኝ አላቸው። አሳልፎ የሰጠውም ይሁዳ ደግሞ **ከእነርሱ ጋር ቆሞ ነበር።**» ዮሃንስ 18፡4-5

ይህ አንቀጽ ደግሞ የሚነግረን ይሁዳ *መጀመሪያውኑ* ለምልክትነት ሊስመው ይቅርና ገና ከነርሱ ጋር ቆሞ በነበረበት ሰዐት ነው እየሱስ በራሱ ምርጫ ማንነቱን የገለጸላቸው።

ጥያቄው፦ ይሁዳ እየሱስን ለምልክትነት ስሞት ነበር ወይንስ አልሳመውም?

14. ስለጴጥሮስ ክህደት እየሱስ በትክክል ምንድን ነበር ያለው?

ስለጴጥሮስ ክህደት እየሱስ በትክክል ምንድን ነበር ያለው?
«ኢየሱስም እንዲህ ብሎ መለሰለት፦ ነፍስህን ስለ እኔ ትሰጣለህን? እውነት እውነት እልሃለሁ፥ ሦስት ጊዜ እስክትክደኝ ድረስ ዶሮ አይጮኽም።ዮሃንስ 13፡38

በዚህ አንቀጽ እንደምንረዳው ዶሮ የሚጮኸው ጴጥሮስ እየሱስን **ሶስት** ጊዜ ከካዳው በኋላ ነው። በሌላ አንቀጽ ደግሞ

"ኢየሱስም፦ እውነት እልሃለሁ፥ ዛሬ በዚች ሌሊት ዶሮ **ሁለት ጊዜ** ሳይጮኽ ሦስት ጊዜ ትክደኛለህ አለው።» ማርቆስ 14፡30

ነገር ግን በመጀመሪያው የዮሀንስ ወንጌል የተጠቀሰው ትንቢት ማለትም ዶሮ የሚጮህው ጴጥሮስ ሶስት ጊዜ እየሱስን ከከዳ በኋላ ነው የሚለውን ሀሳብ ግን ማርቆስ ውድቅ ያደርገዋል ምክንያቱም ዶሮው የጮኸው ገና ጴጥሮስ ሶስት ጊዜ ሳይከዳው ነበር፡፡ ቀጥሎ ያለውን ያለውን የማርቆስ አንቀጽና ከበፊቱ ያሉትን መመልከት ይቻላል

"ጴጥሮስንም ኢየሱስ፦ ዶሮ ሁለት ጊዜ ሳይጮኽ ሦስት ጊዜ ትክደኛለህ ያለው ቃል ትዝ አለው፤ ነገሩንም አስቦ አለቀሰ።» ማርቆስ 14፡72

ጥያቄው፦ የቱ ነው ትክክል?

15. እራሱ ወይንስ ሌላ ሰው?

መስቀሉን የተሸከመው እራሱ እየሱስ ነበር ወይንስ ሌላ ሰው?

"ኢየሱስንም ይዘው ወሰዱት፤ መስቀሉንም **ተሸክሞ** በዕብራይስጥ ጎልጎታ ወደ ተባለው የራስ ቅል ስፍራ ወደሚሉት ወጣ።» ዮሀንስ 19፡17

ይህ አንቀጽ የሚነግረን መስቀሉን የተሸከመው እራሱ እየሱስ እንደነበር ነው፡፡

በሌላ ቦታ ግን እንዲህ እናገኛለን

«ከዘበቱበትም በኋላ ቀዩን ልብስ ገፈፉት፥ ልብሱንም አለበሱት ሊሰቅሉትም ወሰዱት።ሲወጡም **ስምዖን** የተባለው

የቀሬናን ሰው አገኙ፤ እርሱንም መስቀሉን ይሸከም ዘንድ አስገደዱት።» ማቴዎስ 27፡31-32

ይህ አንቀጽ ደግሞ የሚነግረን መስቀሉን የተሸከመው እየሱስ እራሱ ሳይሆን ስምዖን የተባለ የቀሬናን ሰው እንደሆነ ነው።።

ጥያቄው: መስቀሉን የተሸከመው እየሱስ ነበር ወይንስ ስምኦን የተባለ የቀሬናን ሰው?

16. ከመቀደዱ በፊት ነው ወይንስ በኋላ?

እየሱስ የሞተው የቤተ መቅደሱ መጋረጃ ከመቀደዱ በፊት ነው ወይንስ በኋላ?

«ኢየሱስም ሁለተኛ በታላቅ ድምፅ ጮኾ ነፍሱን ተወ። እነሆም፥ የቤተ መቅደስ መጋረጃ ከላይ እስከ ታች ከሁለት ተቀደደ፥ ምድርም ተናወጠች፥ ዓለቶችም ተሰነጠቁ፤» ማቴወስ 27፡50-51

ተመሳሳይ

«ኢየሱስም በታላቅ ድምፅ ጮኸ ነፍሱንም ሰጠ።የቤተ መቅደስም መጋረጃ ከላይ እስከ ታች ከሁለት ተቀደደ።» ማርቆስ 15፡37-38

በነዚህ አንቀጾች የምንረዳው እየሱስ ነፍሱን ከሰጠ በኋላ የቤተ መቅደሱ መጋረጃ እንደተቀደደ ነው።። በሌላ ቦታ ግን ተቃራኒ ነገር እናገኛለን።።

«የቤተ መቅደስም መጋረጃ ከመካከሉ ተቀደደ።ኢየሱስም በታላቅ ድምፅ ጮኾ፦ አባት ሆይ፥ ነፍሴን በእጅህ አደራ እሰጣለሁ አለ። ይህንም ብሎ ነፍሱን ሰጠ።» ሉቃስ 23፡45-46

ይህ አንቀጽ ደግሞ የሚነግረን የቤተ መቅደሱ መጋረጃ ከተቀደደ በኋላ ነው እየሱስ ነፍሱን የሰጠው።።

ጥያቄው፦ እየሱስ የሞተው የቤተመቅደሱ መጋረጃ ከተቀደደ በኋላ ነው ወይንስ በፊት?

17. ነበር ወይንስ አልነበረም?

እየሱስ በስውር የተናገረው ነገር ነበር ወይንስ አልነበረም?

«ኢየሱስም መልሶ፦ እኔ በግልጥ ለዓለም ተናገርሁ፤ አይሁድ ሁሉ በሚሰበሰቡበት በምኵራብና በመቅደስ እኔ ሁልጊዜ አስተማርሁ፥ **በስውርም ምንም አልተናገርሁም**።» የሀንስ 18፡20

ይህ አንቀጽ እንደሚነግረን እየሱስ በግልጽ እንጅ በስውር ምንም ነገር አልተናገረም።።

በሌላ ቦታ ግን ይህንን እናገኛለን

«ለብቻቸውም ሲሆኑ ነገሩን ሁሉ ለገዛ ደቀ መዛሙርቱ ይፈታላቸው ነበር።» ማርቆስ 4፡34

በዚህ አንቀጽ ደግሞ ለደቀመዛሙርቱ ምሳሌዎችን ለብቻቸው በሚሆኑበት ሰአት ይነግራቸውና ይፈታላቸዋል እንደነበር ነው።

በተጨማሪም

«ደቀ መዛሙርቱም ቀርበው፦ ስለ ምን በምሳሌ ትነግራቸዋለህ? አሉት።እርሱም መልሶ እንዲህ አላቸው፦ ለእናንተ የመንግሥተ ሰማያትን ምሥጢር ማወቅ ተሰጥቶአችኋል፥ ለእነርሱ ግን አልተሰጣቸውም።» ማቴወስ 13፡10-11

ጥያቄው፡ለነሱ ምሳሌዎች ካለምንም ምስጢር ግልጽ ይደረግላቸው ከነበረና ለሌሎች ግን ሚስጥር ከነበረ ታዲያ እየሱስ ምንም ያልተናገርኩት ስውር ነገር የለም ሲል ምን ማለቱ ነው?

18. እግዚአብሄር ወይስ ሰይጣን?

ለዳዊት እስራኤልን እንዲቆጥር ያነሳሳው ማነው? እግዚአብሄር ወይስ ሰይጣን?

«ደግሞም **የእግዚአብሔር ቍጣ** በእስራኤል ላይ ነደደ፥ ዳዊትንም፦ ሂድ፥ እስራኤልንና ይሁዳን ቍጠር ብሎ በላያቸው አስነሣው።» መጽሀፈ ሳሙኤል ካልዕ 24፡1

ይህ አንቀጽ በግልጽ እንደሚነግረን ዳዊት እስራኤልና ይሁዳን እንዲቆጥር ያዘዘው እግዚአብሄር ነው፡፡ ነገር ግን

ከዚህ በተቃራኒ በሆነ መልኩ ደግሞ በሌላ ቦታ ላይ ይህንን እናገኛለን፡፡

«**ሰይጣንም በእስራኤል** ላይ ተነሣ፥ እስራኤልንም ይቈጥር ዘንድ ዳዊትን አንቀሳቀሰው።» መጽሀፈ ዜና መዋዕል ቀዳማዊ 21፡1

ይህ አንቀጽ ደግሞ የሚነግረን እስራኤልን ይቆጥረ ዘንድ ዳዊትን ያነሳሳው ሰይጣን እንደሆነ ነው፡፡

ጥያቄው፡- ዳዊት እስራኤልን ይቆጥር ዘንድ ያነሳሳው ማነው?

19. የእስራኤል ተዋጊዎች ብዛት

«ኢዮአብም የሕዝቡን ቁጥር ድምር ለንጉሡ ሰጠ፤ በእስራኤልም ሰይፍ የሚመዝዙ **ስምንት መቶ ሺህ** ጽኑዓን ሰዎች ነበሩ፤ የይሁዳም ሰዎች አምስት መቶ ሺህ ነበሩ።» መጽሀፈ ሳሙኤል ካልዕ 24፡9

በዚህ አንቀጽ የተገለጸው የእስራኤል ተዋጊዎች ብዛት ስምንት መቶ ሺ እንደሆነ ነው፡፡ ነገር ግን ሌላ ቦታ ላይ ደግሞ እንዲህ ይላል፡

«ኢዮአብም የቈጠራቸውን የሕዝቡን ድምር ለዳዊት ሰጠ፤ ከእስራኤልም ሁሉ **አንድ ሚሊዮን ከመቶ ሺህ** ሰይፍ የሚመዝዙ ሰዎችን አገኘ፤ ከይሁዳም አራት መቶ ሰባ ሺህ ሰይፍ የሚመዝዙ ሰዎችን አገኘ።» መጽሀፈ ዜና መዋዕል ቀዳማዊ 21፡5

ከዚህ አንቀጽ እንደምንረዳው ደግሞ የእስራኤል ተዋጊዎች ብዛት አንድ ሚልዮን ከመቶ ሺሕ እንደሆነ ነው፡፡

ጥያቄው፡- የእስራኤላውያን ተዋጊዎች ብዛት ስምንት መቶ ሺ ነው ወይንስ አንድ ሚልዮን አንድ መቶ ሺህ ነው? ይህ አስታራቂ የሌለው ግልጽ ግጭት ነው፡፡

20. የዳዊት ተዋጊዎች ብዛት

ኢዮአብም የሕዝቡን ቁጥር ድምር ለንጉሡ ሰጠ፤ በእስራኤልም ሰይፍ የሚመዝዙ ስምንት መቶ ሺህ ጽኑዓን ሰዎች ነበሩ፤ **የይሁዳም ሰዎች አምስት መቶ ሺህ ነበሩ።**» መጽሀፈ ሳሙኤል ካልዕ 24፡9

በዚህ አንቀጽ የተገለጸው የይሁዳ ተዋጊዎች ብዛት አምስት መቶ ሺ እንደሆነ ነው፡፡ ነገር ግን ሌላ ቦታ ላይ ደግሞ እንዲህ ይላል፡

«ኢዮአብም የቈጠራቸውን የሕዝቡን ድምር ለዳዊት ሰጠ፤ ከእስራኤልም ሁሉ አንድ ሚሊዮን ከመቶ ሺህ ሰይፍ የሚመዝዙ ሰዎችን አገኘ፤ **ከይሁዳም አራት መቶ ሰባ ሺህ** ሰይፍ የሚመዝዙ ሰዎችን አገኘ።»

መጽሀፈ ዜና መዋዕል ቀዳማዊ 21፡5

ከዚህ አንቀጽ እንደምንረዳው ደግሞ የይሁዳ ተዋጊዎች ብዛት አራት መቶ ሰባ ሺህ እንደሆነ ነው፡፡

ጥያቄው :የይሁዳ ተዋጊዎች ብዛት አምስት መቶ ሺ ነው ወይንስ አራት መቶ ሰባ ሺህ ነው? ይህ በተመሳሳይ አስታራቂ የሌለው ግልጽ ግጭት ነው::

21. የስንት አመት ረሀብ?

አምላክ ለዳዊት ነብይ ከላከ በኋላ የስንት አመት ረሀብ አመጣበት?

ጋድም ወደ ዳዊት መጥቶ። እግዚአብሔር እንዲህ ይላል። የምትወድደውን ምረጥ፤ **የሦስት ዓመት ራብ**፥ ወይም ሦስት ወር የጠላቶችህ ሰይፍ እንዲያገኝህ ከጠላቶችህ መሰደድን፥ ወይም ሦስት ቀን የእግዚአብሔር ሰይፍ ቸነፈርም በምድር ላይ መሆንን፥ የእግዚአብሔርም መልአክ በእስራኤል ምድር ሁሉ ማጥፋትን ምረጥ፤ አሁንም ለላከኝ ምን እንድመልስ ተመልከት አለው። መጽሐፈ ዜና መዋዕል ቀዳማዊ 21፥11-12

እዚህ ጋር የተገለጸው የረሀብ ጊዜ ሶስት አመት እንደሆነ ነው ነገር ግን በሌላ አንቀጽ

«ጋድም ወደ ዳዊት መጥቶ፦ የሦስት ዓመት ራብ በአገርህ ላይ ይምጣብህን? ወይስ ጠላቶችህ እያሳደዱህ ሦስት ወር ከእነርሱ ትሸሸን? ወይስ የሦስት ቀን ቸነፈር በአገርህ ላይ ይሁን? አሁንም ለላከኝ ምን መልስ እንደምሰጥ አስብና መርምር ብሎ ነገረው።» መጽሀፈ ሳሙኤል ካልዕ 24፡13

ይህ ክፍል በአማርኛው መጽሀፍ ቅዱስ ውስጥ ሦስት አመት በሚል ተቀምጧል፡፡ የንጉስ ጀምስ ቅጅ/king james version/ ደግሞ እንዲህ ይላል፡-

«So, Gad came to David, and told him, and said unto him, shall seven years of famine come unto thee in thy land? or wilt thou flee three months before thine enemies, while they pursue thee? or that there be three days' pestilence in thy land? now advise, and see what answer I shall return to him that sent me. » 2 Samuel 24:13

በእንግሊዝኛው መጽሀፍ ቅዱሶች ውስጥ የሚገኘው የመጽሀፈ ሳሙኤል ካልእ ሰባት አመት የረሀብ ጊዜ ወደ አማርኛ ሲተረጎም ወደ ሦስት የተቀየረበት ምክንያት እንቆቅልሽ ነው፡፡ ምናልባት ግጭቱን ለማስቀረት የሀገራችን ሊቃውንት የፈጠሩት መላ ይሆን? መጽሀፉን በዚህ መልኩ ይጫወቱበታል፡፡ አላህ እውነቱን ያሳውቃቸው፡፡

22. የአካዝያስ እድሜ

አካዝያስም መንገሥ በጀመረ ጊዜ ዕድሜው **አርባ ሁለት ዓመት ነበረ፥** በኢየሩሳሌምም አንድ ዓመት ነገሠ፤ እናቱም ጎቶሊያ የተባለች የዘንበሪ ልጅ ነበረች።»

መጽሀፈ ዜና መዋዕል ካልዕ 22:2

በዚህ አንቀጽ የአካዝያስ እድሜ አርባ ሁለት እንደሆነ ተገልጸዋል ነገር ግን

«መንገሥ በጀመረ ጊዜ አካዝያስ **የሀያ ሁለት ዓመት** ጕልማሳ ነበረ፤ በኢየሩሳሌምም አንድ ዓመት ነገሠ። እናቱም ጎቶልያ የተባለች የእስራኤል ንጉሥ የዘንበሪ ልጅ ነበረች።2ኛ ነገስት 8፡26

ጥያቄው: አካዝየስ መንገስ በጀመረ ጊዜ እድሜው አርባ ሁለት ነበር ወይንስ ሀያ ሁለት?

23. የዮአኪን ንግስና

«ዮአኪን መንገሥ በጀመረ ጊዜ **የአሥራ ስምንት ዓመት** ጕልማሳ ነበረ፤ በኢየሩሳሌምም ሦስት ወር ነገሠ እናቱም ኔሲታ ትባል ነበር፤ እርስዋም የኢየሩሳሌም ሰው የኤልናታን ልጅ ነበረች።»መጽሀፈ ነገስት ካልዕ 24፡8

ይህ አንቀጽ ዮአኪን መንገስ በጀመረ ጊዜ እድሜው አስራ ስምንት እንደሆነ ይገልጻል ነገር ግን፡-

«ዮአኪንም መንገሥ በጀመረ ጊዜ **የስምንት ዓመት ጕልማሳ** ነበረ፥ በኢየሩሳሌምም ሦስት ወርና አሥር ቀን ነገሠ፤ በእግዚአብሔርም ፊት ክፉ አደረገ።»

መጽሀፈ ዜና መዋዕል ካልዕ 36፡9 (የእንግሊዝኛው የንጉስ ጀምስ /King James/ ቅጅ)

ጥያቄው: ዮአኪን መንገስ በጀመረ ጊዜ እድሜው ስንት ነበር?

የሚገርመው ግን በአማርኛ የቅርብ ጊዜ የትርጉም ሰራዎች ውስጥ ይህ የዜና መዋእል ካለዕ 36፡9 አንቀጽ ላይ

ግጭቱን ለማስቀረት እድሜው አስራ ስምንት በሚል ተስተካክሎ ተቀምጧል! ለምን? እንግሊዝኛው የንጉስ ጀምስ/king James/ ቅጅ ግን ሳይቀያየር አሁን ድረስ እንዲህ ይላል::

« ¶Jehoiachin was eight years old when he began to reign, and he reigned three months and ten days in Jerusalem: and he did that which wasevil in the sight of the Lord.»

2 Chronicles 36:9

ፍርዱን ለህሊና! አብዛኛው ህዝበ ክርስቲያኑ ሊቃውንቱ እንዲህ በቅዱስ መፅሀፉ እየተጫወቱበት እንደሆነ እንኳን አያውቅም፡

24. ዮአኪን በእየሩሳሌም ለምን ያህል ጊዜ ነግሷል?

«..... በኢየሩሳሌምም **ሦስት ወር** ነገሠ እናቱም ኔስታ ትባል ነበር፤ እርስዋም የኢየሩሳሌም ሰው የኤልናታን ልጅ ነበረች።» መጽሀፈ ነገስት ካልዕ 24፡8

በሌላ ቦታ ደግሞ

«.....በኢየሩሳሌምም **ሦስት ወርና አሥር ቀን ነገሠ**፤ በእግዚአብሔርም ፊት ክፉ አደረገ።»

መጽሀፈ ዜና መዋዕል ካልዕ 36፡9

ጥያቄው፡- ዮአኪን በእየሩሳሌም ሦስት ወር ወይንስ ሦስት ወር ከአስር ቀን ነው የነገሰው?

25. የዳዊት ሀያላን አለቃ በአንድ ጊዜ ምን ያህል ሰዎችን ገደለ?

«የዳዊትም ኃያላን ቍጥር ይህ ነበረ፤ የሠላሳው አለቃ የአክሞናዊው ልጅ ያሾብአም ነበረ፤ እርሱ ጦሩን አንሥቶ **ሦስት መቶ ሰው** በአንድ ጊዜ ገደለ።»

መጽሀፈ ዜና መዋዕል ቀዳማዊ ፲፡፲፩

እዚህጋር አለቃው በአንድ ጊዜ የገደላቸው ሦስት መቶ ሰወች እንደሆኑ ተገልጸዋል በሌላ ቦታ ግን

«የዳዊት ኃያላን ስም ይህ ነው። የአለቆች አለቃ የሆነ ከነዓናዊው ኢያቡስቴ ነበረ፤ እርሱም ጦሩን አንሥቶ **ስምንት መቶ** ያህል በአንድ ጊዜ ገደለ።»

መጽሐፈ ሳሙኤል ካልዕ 23፡8

በዚህ አንቀጽ ደግሞ የተገደሉት ሰዎች ብዛት ስምንት መቶ ሰዎች እንደሆኑ ይገልጻል፡፡

ጥያቄ፡- ባንድ ጊዜ የተገደሉት ሰዎች ብዛት ሦስት መቶ ወይንስ ስምንት መቶ ነው?

26. ዳዊትና የእግዚአብሄር ታቦት

ፍልስጤማውያንን ካጠቁ በኋላ (ሙሉ ታሪኩ መጽሐፈ ሳሙኤል ካልዕ ምዕራፍ 5 እና 6 ላይ ይገኛል)

ፍልስጤማውያንን ከማጥቃታቸው በፊት (ሙሉ ታሪኩ ዜና መዋዕል ቀዳማዊ ምዕራፍ 13 እና 14 ይገኛል)

ጥያቄው፡- ዳዊት የእግዚአብሄርን ታቦት ወደ እየሩሳሌም ያመጣው ፍልስጤማውያንን ካጠቃ በኋላ ነው ወይንስ ከማጥቃቱ በፊት?

27. የፍጡራን ብዛት በኖህ መርከብ ውስጥ

«ከአንተ ጋር በሕይወት ይኖሩ ዘንድ ሥጋ ካለው ከሕያው ሁሉ ሁለት ሁለት እያደረግህ ወደ መርከብ ታገባለህ፤ ተባትና እንስት ይሁን፤ከወፍ እንደ ወገኑ፥ ከእንስሳም እንደ ወገኑ፥ ከምድር ተንቀሳቃሽም ሁሉ እንደ ወገኑ በሕይወት ይኖሩ ዘንድ ሁለት ሁለት እየሆኑ ወደ አንተ ይግቡ።»

ዘፍጥረት 6፡19-20

«ከንጹሕ እንስሳ ሁሉ ሰባት ሰባት ተባትና እንስት፥ ንጹሕ ካልሆነ እንስሳም ሁለት ሁለት ተባትና እንስት፥ ከሰማይ ወፍ ደግሞ ሰባት ሰባት ተባትና እንስት እያደረግህ በምድር ላይ ለዘር ይቀር ዘንድ ለአንተ ትወስዳለህ።» ዘፍጥረት 7፡2-3

ጥያቄው፡- የገቡት ሰባት ሰባት እየሆኑ ነው ወይንስ ሁለት ሁለት እየሆኑ?

28. ምርኮኛ ፈረሶች

«ዳዊትም ከእርሱ ሺህ ሰባት መቶ ፈረሰኞች፥ ሀያ ሺህም እግረኞች ያዘ፤ ዳዊትም የሰረገለኛውን ፈረስ ሁሉ ቋንጃ ቈረጠ፤ ለመቶ ሰረገላ ብቻ አስቀረ።»

መጽሐፈ ሳሙኤል ካልዕ 8፡4

ይህ አንቀጽ እንደሚገልጽልን የተማረኩት ፈረሰኞች ብዛት ሺ ሰባት መቶ እንደሆነ ነው፡፡ በሌላ ቦታ ግን እንዲህ ይላል

«ዳዊትም ከእርሱ አንድ ሺህ ሰረገሎች፥ ሰባት ሺህም ፈረሰኞች፥ ሀያ ሺህም እግረኞች ወሰደ፤ ዳዊት ለመቶ ሰረገሎች የሚሆኑትን ብቻ አስቀርቶ የሰረገሎቹን ፈረሶች ቋንጃ ቆረጠ።»

ዜና መዋዕል ቀዳማዊ 18፡4

ይህ አንቀጽ ደግሞ የሚለን የፈረሰኞች ብዛት ሰባት ሺህ እንደሆነ ነው፡፡

ጥያቄው፡- የተማረኩ ፈረሶች ብዛት ሺ ሰባት መቶ ወይንስ ሰባት ሺህ?

29. ሰለሞን ምን ያህል የፈረስ ጋጣች ነበሩት?

«ለሰሎሞንም በአርባ ሺህ ጋጥ የሚገቡ የሰረገላ ፈረሶች አሥራ ሁለትም ሺህ ፈረሰኞች ነበሩት።»

መጽሀፈ ነገስት ቀዳማዊ 4፡26

በሌላ ቦታ ደግሞ

«ሰሎሞንም ለፈረሶችና ለሰረገሎች አራት ሺህ ጋጥ፥ አሥራ ሁለት ሺህም ፈረሰኞች ነበሩት፥ በሰረገሎችም ከተሞች፥ ከንጉሡም ጋር በኢየሩሳሌም አኖራቸው።»

ዜና መዋዕል ካልዕ 9፡25

ጥያቄው፡- የፈረስ ጋጦች አራት ሺህ ነበሩ ወይንስ አርባ ሺህ?

30. የእስራኤል ንጉስ ባአስ

አሳ በነገሰ በስንተኛው አመት ነው የእስራኤል ንጉስ ባአስ በይሁዳ ላይ የወጣው?

«በይሁዳም ንጉሥ በአሳ በሀያ ስድስተኛው ዓመት የባአስ ልጅ ኤላ በእስራኤል ላይ በቴርሳ ሁለት ዓመት ነገሠ።»

መጽሀፈ ነገስት ቀዳማዊ 16፡8

ነገር ግን

«አሳ በነገሠ በሠላሳ ስድስተኛው ዓመት የእስራኤል ንጉሥ፡ባአስ በይሁዳ ላይ ወጣ፥ወደ ይሁዳም ንጉሥ ወደ አሳ ማንም መውጣትና መግባት እንዳይችል ራማን ሠራ።» ዜና መዋዕል ካልዕ 16፡1

ጥያቄው፡- የመጀመሪያው አንቀጽ በሀያ ስድስተኛው አመት ሲል ሁለተኛው አንቀጽ ግን እስከ ሰላሳ ስድስተኛው

አመት ስልጣን ላይ እንደነበረ ይገልጻል። ታዲያ ከዚህ በላይ ግጭት ከወዴት ይገኛል?

31. ለሰለሞን ቤተ-መቅደስ ስራ የተሳተፉ ሰዎች ምን ያህል ናቸው?

«ሰሎሞንም የሚሸከሙትን ሰባ ሺህ፥ከተራሮችም የሚጠርቡትን ሰማኒያ በእነርሱም ላይ የተሾሙትን *ሦስት* ሺህ ስድስት *መቶ* **ሰዎች ቈጠረ።» ዜና መዋዕል ካልእ 2፡2**

በሌላ ቦታ ደግሞ

«besides the chief of Solomon's officers which wereover the work, three thousand and three hundred,which ruled over the people that wrought in the work.»

1 king 5:16

«ሰሎሞንም ሰባ ሺህ ተሸካሚዎች፥ ሰማንያ ሺህም በተራራው ላይ የሚጠርቡጠራቢዎች ነበሩት። ይኸውም በሥራተኛው ሕዝብ ላይ ከተሾሙት **ከሦስት ሺህ ሦስትመቶ**፡ሰዎች፡ሌላ፡ ነው» መጽሀፈ ነገስት ቀዳማዊ 5፡15-16

ጥያቄው፡- ሶስት ሺህ ሶስት መቶ ወይንስ ሶስት ሺ ስድስት መቶ?

ነገር ግን አሁን ላይ እየታተሙ የሚወጡ የአማርኛው መጽሀፍ ቅዱስ ቅጂዎች ከእንግሊዝኛው በተለየ ሁኔታ ሶስት

ሺ ሶስት መቶ ወደ ሶስት ሺ ስድስት መቶ በሚል ቀይረውታል፤ ለምን? የእንግሊዝኛውን የንጉስ ጀምስ ቅጅ ለማጣቀሻነት ከላይ ተቀምጧል።

32. ምን ያህል የባዶስ መስፈሪያ ይይዝ ነበር?

«ውፍረቱም አንድ ጋት ነበረ፤ከንፈሩም እንደ ጽዋ ከንፈር ተሠርቶ እንደ ሱፍ አበባዎች ሆኖ ተከርክሞ ነበር።ሁለት ሺህም የባዶስ መስፈሪያ ይይዝ ነበር።»መጽሀፈ ነገስት ቀዳማዊ 7፡26

ነገር ግን በሌላ ቦታ

" ውፍረቱም አንድ ጋት ያህል ነበረ፤ ከንፈሩም እንደ ጽዋ ከንፈር፥ እንደ ሱፍ አበባ ሆኖ ተሠርቶ ነበር፤ ሦስት ሺህም የባዶስ መሥፈሪያ ይይዝ ነበር። " (መጽሐፈ ዜና መዋዕል ካልዕ 4: 5)

ጥያቄው፡- ብዛቱ ሁለት ሺህ ወይንስ ሶስት ሺህ የባዶስ መስፈሪያ?

33. የፈሐት ሞዐብ ልጆች ብዛት

«ከኢያሱና ከኢዮአብ ልጆች የሆኑ የፈሐት ሞዓብ **ሁለት ሺህ ስምንት መቶ አሥራ ሁለት።**» መጽሀፈ ዕዝራ 2፡6

በሌላ ቦታ ደግሞ

«ከኢያሱና ከኢዮአብ ልጆች የሆኑ የፈሐት ሞዓብ **ሁለት ሺህ ስምንት መቶ አሥራ ስምንት።**» መጽሀፈ ነህሚያ 7፡11

ጥያቄው፡- ከባቢሎናውያን ምርኮ ነጻ ከተደረጉት እስራኤውያን መካከል የፈሐት ሞዐብ ልጆች ምን ያህል ናቸው? 2812 ወይንስ 2818?

34. የዛቱ ልጆች ምን ያህል ናቸው?

«የዛቱዕ ልጆች፥ **ዘጠኝ መቶ አርባ አምስት።**» መጽሀፈ ዕዝራ 2፡8

በሌላ ቦታ ደግሞ

«የዛቱዕ ልጆች፥ **ስምንት መቶ አርባ አምስት።**» መጽሀፈ ነህሚያ 7፡13

ጥያቄው፡- የዛቱዕ ልጆች 945 ወይንስ 845

35. የአዝጋድ ልጆች ስንት ናቸው?

«የዓዝጋድ ልጆች፥ **ሺህ ሁለት መቶ ሀያ ሁለት።**» መጽሀፈ ዕዝራ 2፡12

በሌላ ቦታ ደግሞ

«የዓዝጋድ ልጆች፥ **ሁለት ሺህ ሦስት መቶ ሀያ ሁለት።**» መጽሀፈ ነህሚያ 7፡17

ጥያቄው፡- የአዝጋድ ልጆች 1222 ወይንስ 2322?

36. የአዲን ልጆች ምን ያህል ናቸው?

«የዓዲን ልጆች፥ **አራት መቶ አምሳ አራት።**» መጽሀፈ ዕዝራ 2፡15

በሌላ ቦታ ደግሞ

«የዓዲን ልጆች፥ **ስድስት መቶ አምሳ አምስት።**» መጽሃፈ ነህሚያ 7፡20

ጥያቄው፡- የዓዲን ልጆች 454 ወይንስ 655

37. የሀሱም ልጆች ምን ያህል ናቸው?

«የሐሱም ልጆች፥ **ሁለት መቶ ሀያ ሦስት።**» መጽሃፈ ዕዝራ 2፡19

በሌላ ቦታ ደግሞ

«የሐሱም ልጆች፥ **ሦስት መቶ ሀያ ስምንት።**» መጽሀፈ ነህሚያ 7፡22

ጥያቄው፡- የሀሱም ልጆች 223 ወይንስ 328

38. የቤቴልና የጋይ ሰዎች ምን ያህል ናቸው?

«የቤቴልና የጋይ ሰዎች፥ ሁለት መቶ ሀያ ሦስት።» መጽሃፈ ዕዝራ 2፡28

በሌላ ቦታ ደግሞ

«የቤቴልና የጋይ ሰዎች፥ መቶ ሀያ ሦስት።» መጽሀፈ ነህሚያ 7፡32

ጥያቄው፡- የቤቴልና የጋይ ሰዎች 223 ወይንስ 123

39. የጉባኤው ብዛት

በጠቅላላ የነበሩ የጉባኤው አባላትን ብዛት አስመልክቶ መጽሀፈ ዕዝራ 2፡64 እና ነህሚያ 7፡66 ሁለቶችም ጠቅላላ ድምራቸው 42,360 እንደሆነ ይስማማሉ ነገር ግን የእያንደንዳቸውን ጠቅላላ ድምር ብንሰራ

መጽሀፈ ዕዝራ =29818

መጽሀፈ ነህሚያ =31089

ጥያቄው፡- ከዚህ በላይ እርስ በርስ መላተም ከወዴት ይገኛል?

40. ምን ያህል መዘምራን ነበሩ?

«ሰባት ሺህ ሦስት መቶ ሠላሳ ሰባት ከነበሩከሎሌዎቻቸውና ከገረዶቻቸውሌላ ጉባኤው ሁሉ አርባ ሁለት ሺህሦስት መቶ ስድሳ ነበሩ። **ሁለት መቶም** ወንዶችና ሴቶች መዘምራን ነበሩአቸው።"

መጽሀፈ ዕዝራ 2፡64-65

በሌላ ቦታ ደግሞ

«ሰባት ሺህ ሦስት መቶ ሠላሳ ሰባት ከነበሩከሎሌዎቻቸውና ከገረዶቻቸው ጉባኤው ሁሉ አርባ ሁለት ሺህ ሦስት መቶ ስድሳ ነበሩ፤ **ሁለቱ መቶም አርባ አምስት** ወንዶችና ሴቶች መዘምራን ነበሩአቸው።» መጽሀፈ ነህሚያ 7፡66-67

ጥያቄው፡- መዘምራኑ 200 ነበሩ ወይንስ 245

41. የንጉስ አብያ እናት ስም ማን ነበር?

«ሦስት ዓመት በኢየሩሳሌም ነገሠ፤ የእናቱም ስም ሚካያ ነበረ፥የገብዓ ሰው የኡርኤል ልጅ ነበረች።» መጽሀፈ ዜና መዋዕል ካልዕ 13፡2

በሌላ ቦታ ግን

«ከእርስዋም በኋላ የአቤሴሎምን ልጅ መዓካን አገባ፤ እርስዋም አብያን፥ ዓታይን፥ዚዛን፥ ሰሎሚትን ወለደችለት።» መጽሀፈ ዜና መዋዕል ካልዕ 11፡20

ነገር ግን ሌላ ቦታ ደግሞ አቤሴሎም አንድ ሴት ልጅ ብቻ እንዳለችውና ኢሷም ትዕማር እንደምትባል ይገልጻል።

«ለአቤሴሎምም ሦስት ወንዶች ልጆችና አንዲት ሴት ልጅ ተወለዱለት፤የሴቲቱም ልጅ ስም ትዕማር ነበረ፥እርስዋም የተዋበች ሴት ነበረች።መጽሀፈ ሳሙኤል ካልዕ 14፡27

ጥያቄው፡- የቱ ነው ትክክል?

<u>42. እያሱና እስራኤላውያን በርግጥ እየሩሳሌምን ተቆጣጥረዋልን?</u>

አዎ!!!!!

ዝርዝር ታሪኩ መጽሀፈ እያሱ 10፡23-40 ላይ ይገኛል

ነገር ግን በሌላ ቦታ እንዲህ ይላል

«በኢየሩሳሌም የተቀመጡትን ኢያቡሳውያንን ግን የይሁዳ ልጆች ሊያሳድዱአቸው አልተቻላቸውም፤ ኢያቡሳውያንም እስከ ዛሬ በይሁዳ ልጆች መካከል ውስጥ ተቀምጠዋል።»

መጽሐፈ ኢያሱ ወልደ ነዌ 15፡63

ጥያቄው፡- እያሱና እስራኤላውያን እየሩሳሌምን ተቆጣጥረዋል ወይንስ አልተቆጣጠሩም?

<u>43. የማርያም እጮኛ የነበረው ዮሴፍ አባቱ ማን ነበር?</u>

«**ያዕቆብም** ክርስቶስ የተባለውን ኢየሱስን የወለደች የማርያምን እጮኛ ዮሴፍን ወለደ።» ማቴወስ 1፡16

በዚህ አንቀጽ እንደተገለጸው የማርያም እጮኛ የነበረው ዮሴፍ የአባቱ ስም ያአቆብ ነው፡፡ ነገር ግን በሌላ ቦታ እንዲህ ይላል፡፡

«ኢየሱስም ሊያስተምር ሲጀምር ዕድሜው ሠላሳ ዓመት ያህል ሆኖት ነበር እንደመሰላቸው የዮሴፍ ልጅ ሆኖ፥ **የኤሊ ልጅ፥**" ሉቃስ 3፡23

በዚህ አንቀጽ ደግሞ እንደተገለጸው የዮሴፍ አባት ኤሊ እንደሆነ ነው፡፡

ጥያቄው፡- የዮሴፍ አባት ያዕቆብ ነው ወይንስ ኤሊ?

44. እየሱስ ከየትኛው የዳዊት ዘር የተገኘ ነው?

«እሴይም ንጉሥ ዳዊትን ወለደ።ንጉሥ ዳዊትም ከኦርዮ ሚስት ሰሎሞንን ወለደ፤ ፤ሰሎሞንም ሮብዓምን ወለደ፤ ሮብዓምም አቢያን ወለደ፤አቢያም አሣፍን ወለደ፤» ማቴዎስ ፩፡ 6-7

በማቴወስ አገላለጽ መሰረት እየሱስ ከሰለሞን በተገኘው የዳዊት ዘር የተገኘ ነው፡፡ ነገር ግን ሉቃስ እንዲህ ይላል

«የዮናን ልጅ፥ የኤልያቄም ልጅ፥የሜልያ ልጅ፥ የማይናን ልጅ፥የማጣት ልጅ፥ የናታን ልጅ»

ሉቃስ 3፡31

በሉቃስ አገላለጽ መሰረት ደግሞ የእየሱስ የዘር ሀረግ የዳዊት ልጅ በሆነው በናታን በኩል ነው፡፡

ጥያቄው፡- እየሱስ በየትኛው የዳዊት ልጅ ሀረግ ውስጥ የተገኘ ነው?

45. የሶላትያል አባት ማን ነው?

«ከባቢሎንም ምርኮ በኋላ **ኢኮንያን**፡ሰላትያልን ወለደ፤ ሰላትያልም ዘሩባቤልን ወለደ፤» ማቴወስ1፡12

በዚህ አንቀጽ መሰረት የሶላትያል አባት አኮንያን ነው፡፡ ነገር ግን ሉቃስ እንዲህ ይላል

«የዮዳ ልጅ፥ የዮናን ልጅ፥ የሬስ ልጅ፥ የዘሩባቤል ልጅ፥ የሰላትያል ልጅ፥ **የኔሪ** ልጅ፥» ሉቃስ 3፡27

ይህ አንቀጽ ደግሞ የሚነግረን የሶላትያል አባት ኔሪ እንደሆነ ነው፡፡

ጥያቄው፡- የሰላትያል አባት ማነው? የሚል ይሆናል፡፡

<u>46. የየትኛው የዘሩባቤል ልጅ ነው የእየሱስ ቅድመ አያት?</u>

«ዘሩባቤልም አብዩድን ወለደ፤ አብዩድም ኤልያቄምን ወለደ፤ ኤልያቄምም አዛርን ወለደ፤» ማቴዎስ 1፡13

በዚህ አንቀጽ የእየሱስ የዘር ሀረግ የሚመዘዘው ከዘሩባቤል ልጅ ከአብዮድ ነው፡፡ ነገር ግን በሌላ ቦታ

«የዮዳ ልጅ፥ የዮናን ልጅ፥ የሬስ ልጅ፥ የዘሩባቤል ልጅ፥ የሰላትያል ልጅ፥ የኔሪ ልጅ፥» ሉቃስ 3፡27

ይህ አንቀጽ ደግሞ በተለየ መልኩ የሚነግረን የእየሱስ የዘር ሀረግ የሚመዘዘው ከዘሩባቤል ልጅ ከሬስ እንደሆነ ነው፡፡

ጥያቄው፡- ከየትኛው የዘሩባቤል ልጅ ነው የእየሡስ ቅድመ አያት የሚመዘዘው?

ከዚህ በተጨማሪ በነኛ ዜና መዋዕል 3፡19-20 እንደተገለጸው

«የፈዳያ ልጆች ዘሩባቤልና ሰሜኢ ነበሩ፤ የዘሩባቤልም ልጆች፤ሜሱላም ሐናንያ እኅታቸውም ሰሎሚት ሐሹባ ኦሄል በራክያ ሐሳድያ ዮሻብሐሴድ ዐምስት ናቸው።»

ከነኝህ የዘሩባቤል ልጆች መካከል ከላይ በእየሱስ የዘር ሀረግ የተጠቀሱት አብዩድና ኔሪ አይገኙም ታዲያ እነኝህ

ሰዎች የት የመጡ ናቸው?

47. የዖዝያን አባት ማነው?

«አሣፍም ኢዮሣፍጥን ወለደ፤ ኢዮሣፍጥም **ኢዮራምን** ወለደ፤ ኢዮራምም ዖዝያንን ወለደ፤» ማቴወስ 1፡8

በዚህ አንቀጽ እንደተገለጸው የዖዝያን አባት እዮራም እንደሆነ ነው፡፡ ነገር ግን በሌላ ቦታ እንዲህ ይላል

«የይሁዳም ሕዝብ ሁሉ የአሥራ ስድስት ዓመትጕልማሳ የነበረውን ዖዝያንን ወስደው በአባቱ **በአሜስያስ** ፋንታ አነገሡት።»

2ኛ ዜና መዋዕል 26፡1

በዚህ አንቀጽ ደግሞ እንደምናየው የዖዝያን አባት አሜስያስ እንደሆነ ነው፡፡

ጥያቄው፡- የዖዝያን አባት ኢዮራም ነው ወይንስ አሜስያ?

48. የኢኮንያ አባት ማነው?

«አሞፅም ኢዮስያስን ወለደ፤ **ኢዮስያስም** በባቢሎን ምርኮ ጊዜ ኢኮንያንንና ወንድሞቹን ወለደ።» ማቴወስ 1፡11

በዚህ አንቀጽ እንደተገለጸው የኢኮንያን አባት ኢዮስያስ እንደሆነ ነው፡፡ ነገር ግን በሌላ ቦታ እንዲህ ይላል

«የኢዮአቄምም ልጆቹ፤ ልጁ ኢኮንያን፥ ልጁ ሴዴቅያስ።» ዜና መዋዕል ቀዳማዊ 3፡16

በዚህ አንቀጽ ደግሞ የኢኮንያ አባት ኢዮአቄም እንደሆነ ይገልጻል፡፡

ጥያቄየው፡- የኢኮንያ አባት ማነው? የሚል ነው

49. ከዳዊት እስከ ባቢሎን ምርኮ ምን ያህል ትውልድ ነው?

«እንግዲህ ትውልድ ሁሉ ከአብርሃም እስከ ዳዊት አሥራ አራት ትውልድከዳዊትም እስከ ባቢሎን ምርኮአሥራ አራት ትውልድ፥ ከባቢሎንም ምርኮ እስከ ክርስቶስ አሥራ አራት ትውልድ ነው።" ማቴወስ 1፡17

በዚህ አንቀጽ እንደተገለጸው ከዳዊት እስከ ባቢሎን አስራ አራት ትውልድ እንደሆነ ነው፡፡ ነገር ግን በማቴወስ 1፡12-16 ያለውን በጥንቃቄ ስንቆጥረው 13 ብቻ ይሆናል፡፡

ጥያቄው፡- ታዲያ ከዳዊት እስከ ባቢሎን ምርኮ ያለው ትውልድ 13 ነው ወይንስ 14?

50. የሳላ አባት ማነው?

«የናኮር ልጅ፥ የሴሮህ ልጅ፥ የራጋው ልጅ፥ የፋሌቅ ልጅ፥ የአቤር ልጅ፥ የሳላ ልጅ፥**የቃይንም** ልጅ፥ የአርፋክስድ ልጅ፥ የሴም ልጅ፥ የኖኅ ልጅ፥ የላሜህ ልጅ፥» ሉቃስ 3፡35-36

በዚህ አንቀጽ እንደተገለጸው የሳላ አባት ቃየን እንደሆነ ነው፡፡ ነገር ግን በሌላ ቦታ እንዲህ ይላል፡፡

«**አርፋክስድም**፡መቶ፡ሠላሳ፡ዐምስት፡ዓመት፡ኖረ፥ሳላን፡ ወለደ» ዘፍጥረት 11፡12

ይህ አንቀጽ የሚነግረን ደግሞ የሳላ አባት አርፋክስድ እንደሆነ ነው፡፡

ጥያቄው፡- የሳላ አባት ማነው?

የቅርብ ጊዜ የአማርኛ መጽሀፍ ቅዱሳን ሳላ በሚለው ቦታ ቃይንምን በመተካት ስህተቱን ለማረም ሞክረዋል። ነገር ግን የየትኛውም ታዋቂ የእንግሊዝኛ ቅጅዎች ይህን ማስተካከያ አይጠቀሙም። ለአብነት የንጉሰ ጀምስ ቅጅን /king james version/ እንመልከት፡፡

«And Arphaxad lived five and thirty years, and begat Salah» Genesis 11:12

ታዲያ የኛ ሀገር ተርጓሚዎች የቃላት ማስተካከያ ማድረጋቸው ስህተቱን ለመሸፈን ይሆን? ሰው እንዴት ራሱን ይሸውዳል? የአለማቱ ጌታ አላህ ልቦና ይስጠን!!!! አሚን

51. ሁለቱም ወይንስ አንዱ?

ወንጌላት እንደሚነግሩን ከእየሱስ ጋር ሁለት ወንበዴዎች አብረው ታስረው ነበር። ታዲያ በእየሱስ ያሾፉት ሁለቱም ነበሩ? ወይንስ አንዱ?

«አይተን እናምን ዘንድ የእስራኤል ንጉሥ ክርስቶስ አሁን ከመስቀል ይውረድ አሉ። **ከእርሱም ጋር የተሰቀሉት ይነቅፉት ነበር።**» ማርቆስ 15:32

በዚህ አንቀጽ እንደተገለጸው ከርሱ ጋ ተሰቀሉ የተባሉት ሁለቱ ወንበዴዎች ይነቅፉት እንደነበር ነው። በሌላ ቦታ ግን እንዲህ ይላል።

«ኢየሱስንም፦ ጌታ ሆይ፥ **በመንግሥትህ በመጣህ ጊዜ አስበኝ አለው።ኢየሱስም፦ እውነት እልሃለሁ፥ ዛሬ ከእኔ ጋር በገነት ትሆናለህ አለው።**»ሉቃስ 23:42-43

በመጀመሪያው አንቀጽ ይነቅፉት ነበር በሚል ሁለቱንም ሲገልጽ በሉቃስ ወንጌል ግን ይነቅፈው የነበረ እንዱ ብቻ እንደነበር ተጠቅሷል።

ጥያቄው፡- ይነቅፉት የነበሩ ሁለቱም ናቸው ወይንስ አንዱ ብቻ ነበር?

52. እየሱስን በሰቀሉት ጊዜ ስንት ሰዐት ነበር?

«በሰቀሉትም ጊዜ **ሦስት ሰዓት** ነበረ።» ማርቆስ 15፡25

በሌላ ቦታ ደግሞ

«ለፋሲካም የማዘጋጀት ቀን ነበረ፤ **ስድስት ሰዓትም** የሚያህል ነበረ፤አይሁድንም፡- እነሆ ንጉሣችሁ አላቸው። ዮሀንስ 19፡14

ጥያቄው፡- እየሱስ በሶስት ሰዐት ከተሰቀለ እንዴት በስድስት ሰዐት ለፍርድ ጲላጦስ ፊት ሊቀርብ ቻለ የሚል ነው፡

53. እየሱስ በተሰቀለበት ቀን ወደ መንግስተ ሰማያት ገብቷልን?

«ኢየሱስም፡- እውነት እልሃለሁ፥ ዛሬ ከእኔ ጋር በገነት ትሆናለህ አለው።» ሉቃስ 23፡43

ይህ አንቀጽ እንደሚነግረን እየሱስ አብሮት ለተሰቀለው ሰው <<ዛሬ>> በገነት እንሆናለን እንዳለው ነው፡፡ ነገር ግን በሌላ ቦታ እየሱስ ይህን ካለ ከሁለት ቀን በኋላ እንዲህ ሲል እንሰማዋለን፡፡

«ኢየሱስም፡- ገና ወደ አባቴ አላረግሁምና አትንኪኝ፤ነገር ግን ወደ ወንድሞቼ ሄደሽ፡-እኔ ወደ አባቴና ወደ አባታችሁ

ወደ አምላኬና ወደ አምላካቸሁ ዓርጋለሁ ብለሽ ንገሪአቸው አላት።" ዮሀንስ20፡17

ጥያቄው፡- እየሱስ የሞተ ቀን ገነት ገብቷል ወይንስ ከሞተ ከሁለት ቀን በኋላ እንኳን ጭራሽ ወደ አባቱም አላረገም?

54. አብረው የነበሩ ሰዎች

ጳውሎስ ወደ ደማስቆ ባደረገው ጉዞ ድምጽና ብርሀን አጋጥሞታል እርሱም ድምጹን ሰምቷል ብርሀኑንንም አይቷል፡፡ ነገር ግን አብረው የነበሩት ሰዎች ድምጹን ሰምተዋልን?

«ከእርሱም ጋር በመንገድ የሄዱ ሰዎች ድምፁንእየሰሙ ማንን ግን ሳያዩ እንደ ዲዳዎች ቆሙ።» የሀዋርያት ስራ 9፡7

በዚህ አንቀጽ እንደተገለጸው ከርሱ ጋር አብረው የነበሩ ሰዎች ማንንም ማየት ባይችሉም ድምጹን ግን ሰምተዋል፡፡ በሌላ ቦታ ግን ይህንን እናገኛለን፡፡

«ከእኔ ጋር የነበሩትም ብርሃኑን አይተው ፈሩ፥ የሚናገረኝን የእርሱን ድምፅ ግን አልሰሙም።» የሀዋርያት ስራ 22፡9

የሚገርመው አቀራረቡ እራሱ ፍጹም ተቃራኒ ነው፡፡ የመጀመርያው ድምጹን ሰምተዋል ሲል የሁለተኛው አንቀጽ ደምጹን አልሰሙም ይላል፡፡ በተመሳሳይ የመጀመርያው አንቀጽ ምንም ነገር እንዳላዩ ሲገልጽ የሁለተኛው ደግም

ብርሀን እንዳዩ ይገልጻል። ገራሚ ነው። ግጭት ቢሉ ግጭት!!

55. ወድቀዋል ወይንስ አልወደቁም?

ጳውሎስ ብርሀኑን ባየ ጊዜ ወድቋል። ከርሱ ጋር የነበሩትስ አብረው ወድቀዋል ወይንስ አልወደቁም?

«ሁላችንም በምድር ላይ በወደቅን ጊዜ፡-ሳውል ሳውል፥ ስለ ምን ታሳድደኛለህ?የመውጊያውን ብረት ብትቃወም ለአንተ ይብስብሃል፡የሚል ድምፅ በዕብራይስጥ ቋንቋ ሲናገረኝ ሰማሁ።»

የሀዋርያት ስራ 26፡14

በዚህ አንቀጽ እንደተገለጸው አብረውት የነበሩትም ጭምር ወደ ምድር ወድቀዋል። በሌላ ቦታ ደግሞ ይህንን እናገኛለን።

«ከእርሱም ጋር በመንገድ የሄዱ ሰዎች ድምፁን እየሰሙ፡ ማንን ግን ሳያዩ እንደ ዲዳዎች ቆሙ።ሳውልም ከምድር ተነሣ፥ አይኖቹም በተከፈቱ ጊዜምንም አላየም፤ እጁንም ይዘው እየመሩ ወደ ደማስቆ አገቡት።» የሀዋርያት ስራ 9፡7-8

ጥያቄው፡- አብረው የነበሩትስ ወድቃዋል ወይንስ ቁመው ነው የቀሩት?

56. የ«ራዕዩ» ድምጽ ጳውሎስ ምን መስራት እንዳለበት ነግሮታልን?

«ነገር ግን ተነሣና በእግርህ ቁም፤ስለዚህ እኔን ባየህበት ነገር ለአንተም በምታይበትነገር አገልጋይና ምስክር ትሆን ዘንድ ልሾምህ ታይቼልሃለሁና።የኃጢአትንም ስርየት በእኔም በማመን፡በተቀደሱት መካከል ርስትን ያገኙ ዘንድ፥ከጨለማ ወደ ብርሃን ከሰይጣንም ሥልጣን ወደ እግዚአብሔር ዘወር እንዲሉ፡ዓይናቸውን ትከፍት ዘንድ፥ ከሕዝቡና ወደ እነርሱ ከምልክህ ከአሕዛብ አድንሃለሁ።" የሀዋርያት ስራ 26፡16-18

በዚህ አንቀጽ ጳውሎስ ምን መስራት እንዳለበት ሳይቀር በራዕይ ድምጹ እራሱ እንደነገረው እንመለከታለን፡፡

እዚያው የሀዋርያት ስራ ሌላ አንቀጽ ላይ ግን ወደ ደማስቆ ይሄድና ስራውን ሰዎች እዚያው እንደሚነግሩት ይገልጻል፡፡

«ከእርሱም ጋር በመንገድ የሄዱ ሰዎች ድምፁን እየሰሙ ማንን ግን ሳያዩ እንደ ዲዳዎች ቆሙ። ሳውልም ከምድር ተነሣ፥ አይኖቹም በተከፈቱ ጊዜ ምንም አላየም፤ እጁንም ይዘው እየመሩ ወደ ደማስቆ አገቡት።» የሀዋርያት ስራ 9፡7-8

ተመሳሳይ

«ጌታ ሆይ፥ ምን ላድርግ? አልሁት።ጌታም፡- ተነሥተህ ወደ ደማስቆ ሂድና ታደርገው ዘንድ ስለ ታዘዘው ሁሉን በዚያ ይነግሩሃል አለኝ።ከዚያ ብርሃንም ክብር የተነሣ ማየት

ባይሆንልኝ ከእኔ ጋር የነበሩት ሰዎች እጇን ይዘው እየመሩኝ ወደ ደማስቆ ደረስሁ።" የሀዋርያት ስራ 22፡10

ጥያቄው፡-ለጳውሎስ ምን ማድረግ እንዳለበት ድምጹ ቀጥታ ነው የነገረው ወይንስ ወደ ደማስቆ እንዲሄድና እዚያ እንዲሰማ ነው ያዘዘው?

57. በመቅሰፍት የሞተው ሰው ብዛት ስንት ነው?

(ኦሪት ዘኁልቁ 25)

1፤ እስራኤልም በሰጢም ተቀመጡ፤ ሕዝቡም ከሞዓብ ልጆች ጋር ያመነዝሩ ጀመር።

2፤ ሕዝቡንም ወደ አምላኮቻቸው መሥዋዕት ጠሩ፤ ሕዝቡም በሉ፥ ወደ አምላኮቻቸውም ሰገዱ።

3፤ እስራኤልም ብዔልፌጎርን ተከተለ፤ የእግዚአብሔርም ቍጣ በእስራኤል ላይ ነደደ።

4፤ እግዚአብሔርም ሙሴን። የእግዚአብሔር የቍጣው ጽናት ከእስራኤል እንዲመለስ የሕዝቡን አለቆች ሁሉ ወስደህ በፀሐዩ ፊት ወደ እግዚአብሔር ስቀላቸው አለው።

5፤ ሙሴም የእስራኤልን ዳኞች። እናንተ ሁሉ ብዔልፌጎርን የተከተሉትን ሰዎቻችሁን ግደሉ አላቸው።

6፤ እነሆም፥ ከእስራኤል ልጆች አንዱ መጥቶ በሙሴና በእስራኤል ልጆች ማኅበር ሁሉ ፊት ምድያማዊቱን አንዲቱን

ሴት ወደ ወንድሞቹ አመጣት፤ እነርሱም በመገናኛው ድንኳን ደጃፍ ያለቅሱ ነበር።

7፤ የካህኑም የአሮን ልጅ የአልዓዛር ልጅ ፊንሐስ ባየው ጊዜ ከማኅበሩ መካከል ተነሥቶ በእጁ ጦር አነሣ፤

8፤ ያንንም የእስራኤልን ሰው ተከትሎ ወደ ድንኳኑ ገባ። እስራኤላዊውንም ሰውና ሴቲቱን ሁለቱን ሆዳቸውን ወጋቸው። ከእስራኤልም ልጆች መቅሠፍቱ ተከለከለ።

9፤ በመቅሠፍትም የሞተው ሀያ አራት ሺህ ነበረ።

በዚህ አንቀጽ እንደተገለጸው የሟቾች ቁጥረ **ሀያ አራት ሺህ** ነው::

በሌላ ቦታ ግን ይህን እናገኛለን::

"ከእነርሱም አንዳንዶቹ እንደ ሴሰኑ በአንድ ቀንም ሁለት እልፍ ከሦስት ሺህ እንደ ወደቁ አንሴስን። " (ነኛ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 10: 8)

ይህ አንቀጽ ደግሞ የሚነግረን ደግሞ የሟቾች ቁጥር **ሀያ ሶስት ሺ** እንደሆነ ነው::

ጥያቄው፡- የሟቾች ቁጥር ሀያ አራት ሺ ነበር ወይንስ ሀያ ሶስት ሺ?

58. ወደ ግብጽ የገቡት የያዕቆብ ቤተሰቦች ምን ያህል ናቸው?

"፤ በግብፅ ምድር የተወለዱለት የዮሴፍም ልጆች ሁለት ናቸው፤ ወደ ግብፅ የገቡት የያዕቆብ ቤተ ሰዎች ሁሉ **ሰባ** ናቸው። "

(ኦሪት ዘፍጥረት 46: 27)

ይህ አንቀጽ የሚነግረን የያዕቆብ ቤተሰቦች ብዛት በጠቅላላ ሰባ እንደሆነ ነው። ነገር ግን በሌላ ቦታ እንዲህ ይላል፡

"፤ ዮሴፍም አባቱን ያዕቆብንና **ሰባ አምስት** ነፍስ የነበረውን ቤተ ዘመድ ሁሉ ልኮ አስጠራ። "

(የሐዋርያት ሥራ 7: 14)

ይህ አንቀጽ ደግሞ የሚነግረን ብዛታቸው ሰባ አምስት እንደሆነ ነው።

ጥያቄው፡- ወደ ግብጽ የገቡት የያዕቆብ ቤተሰቦች ብዛት ሰባ ነው ወይንስ ሰባ አምስት?

59. ይሁዳ እየሱስን በመክዳቱ ያገኘውን ገንዘብ ምን አደረገው?

"ይህም ሰው በዓመፅ ዋጋ መሬት ገዛ በግንባሩም ተደፍቶ ከመካከሉ ተሰነጠቀ አንጀቱም ሁሉ ተዘረገፈ፤ "

(የሐዋርያት ሥራ 1: 18)

አንቀጹ በግልጽ እንደሚነግረን ይሁዳ በብሩ መሬት እንደገዛ ነው:: ነገር ግን በተቃራኒው ሌላ ቦታ ደግሞ ይህንን እናገኛለን::

"ብሩንም በቤተ መቅደስ ጥሎ ሄደና ታንቆ ሞተ። "

(የማቴዎስ ወንጌል 27: 5)

ታዲያ ጥያቄው ይሁዳ ያገኘውን ገንዘብ መሬት ነው የገዛበት ወይንስ ቤተ-መቅደስ ነው ጥሎት የሄደው?

60. ይሁዳ እንዴት ሞተ?

"ብሩንም በቤተ መቅደስ ጥሎ ሄደና **ታንቆ ሞተ።** "

(የማቴዎስ ወንጌል 27: 5)

የይሁዳን አሟሟት ማቴዎስ የሚነግረን ታንቆ እንደሞተ ነው:: ነገር ግን በሌላ ቦታ እንዲህ ይላል

"ይህም ሰው በዓመፅ ዋጋ መሬት ገዛ **በግንባሩም ተደፍቶ ከመካከሉ ተሰነጠቀ አንጀቱም ሁሉ ተዘረገፈ** "

(የሐዋርያት ሥራ 1: 18)

ይህኛው አንቀጽ ደግሞ በግንባሩ ተደፍቶና አንጀቱ ተዘርግፎ አንደሞተ ይገልጻል::

ጥያቄው፡- ይሁዳ ታንቆ ነው የሞተው ወይንስ በግንባሩ ተደፍቶና ሆዱ ተዘርግፎ ነው የሞተው?

61. የደም መሬት የተባለው ለምንድን ነው?

(የማቴዎስ ወንጌል 27)

5፤ ብሩንም በቤተ መቅደስ ጥሎ ሄደና ታንቆ ሞተ።

6፤ የካህናት አለቆችም ብሩን አንሥተው። የደም ዋጋ ነውና ወደ መባ ልንጨምረው አልተፈቀደም አሉ።

7፤ ተማክረውም የሸክላ ሠሪውን መሬት ለእንግዶች መቃብር ገዙበት።

8፤ ስለዚህ ያ መሬት እስከ ዛሬ ድረስ የደም መሬት ተባለ።

ይህ አንቀጽ እንደሚነግረን የደም መሬት የተባለበት ምክንያት ዋጋው የደም ዋጋ ስለነበር ነው፡፡ ከዚህ በተለየ ግን ሌላ ቦታ ደግሞ የተለየ ሀሳብ እናገኛለን

(የሐዋርያት ሥራ ፩)

18፤ ይህም ሰው በዓመፅ ዋጋ መሬት ገዛ በግንባሩም ተደፍቶ ከመካከሉ ተሰነጠቀ አንጀቱም ሁሉ ተዘረገፈ፤

19፤ በኢየሩሳሌምም ለሚኖሩ ሁሉ ታወቀ፤ ስለዚህም ያ መሬት በቋንቋቸው አኬልዳማ ተብሎ ተጠራ፥ እርሱም የደም መሬት ማለት ነው።

ይህ አንቀጽ ደግሞ የሚነግረን ቦታው ላይ ይሁዳ በመሞቱና ደሙ በመፍሰሱ ምክንያት የደም መሬት እንደተባለ ነው።።

ጥያቄው፦ ቦታው የደም መሬት የተባለበት ምክንያት መሬት የተገዛበት ቦታ የደም ዋጋ ስለሆነ ነው ወይንስ መሬቱ ላይ ይሁዳ ስለሞተበት ነው?

62. ማን ለማን ቤዛ ነው?

"እንዲሁ የሰው ልጅም ሊያገለግልና ነፍሱን ለብዙዎች ቤዛ ሊሰጥ እንጂ እንዲያገለግሉት አልመጣም። "

(የማርቆስ ወንጌል 10: 45)

በተመሳሳይም

(1ኛ ወደ ጢሞቴዎስ 2)

5፤ አንድ እግዚአብሔር አለና፥ በእግዚአብሔርና በሰውም መካከል ያለው መካከለኛው ደግሞ አንድ አለ፥ እርሱም ሰው የሆነ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው፤

6፤ ራሱንም ለሁሉ ቤዛ ሰጠ፥ ይህም በገዛ ዘመኑ ምስክርነቱ ነበረ፤

ከላይ ያየናቸው አንቀጾች የሚነግሩን እየሱስ የመጣው ለሰው ልጅ ቤዛ ለመሆን ነው።። ነገር ግን በሌላ ቦታ ስናነብ ይህንን እናገኛለን

«ኃጥእ የጻድቅ ቤዛ ነው፤በደለኛም የቅን ሰው ቤዛ ነው።» መጽሀፈ ምሳሌ 21፡18

ጥያቄው፡- እየሱስ ቤዛ የሆነው ሀጥያተኛ ሆኖ ለጻድቅ ሰው ነው ወይንስ በደለኛ ሆኖ ለቅን ነው?

63. የሙሴ ህግ ጠቃሚ ነውን?

"የእግዚአብሔር ሰው ፍጹምና ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ፥ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሣጽ ልብንም ለማቅናት በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል። (2ኛ ወደ ጢሞቴዎስ 3: 16-17)

በዚህ አንቀጽ እንደምንረዳው የእግዚአብሄር መንፈስ ያለበት ማንኛውም መጽሀፍ የሙሴን ህግ ጨምሮ ጠቃሚ ነው፡፡

ነገር ግን በሌላ ቦታ ይህንን እናገኛለን፡፡

"ሕጉ ምንም ፍጹም አላደረገምና፥ ስለዚህም የምትደክም የማትጠቅምም ስለሆነች የቀደመች ትእዛዝ ተሽራለችና፥ ወደ እግዚአብሔርም የምንቀርብበት የሚሻል ተስፋ ገብቶአል። " (ወደ ዕብራውያን 7: 18-19)

ይህ አንቀጽ ደግሞ ህጉ ስለማይጠቅም እንደተሻረ ይገልጻል፡፡

ጥያቄው፡- ህጉ ይጠቅማል ወይንስ አይጠቅምም?

64. የሙሴ ህግ ተሸሯል ወይንስ አልተሻረም?

(የማቴዎስ ወንጌል 5)

17፤ እኔ ሕግንና ነቢያትን ለመሻር የመጣሁ አይምሰላችሁ፤ ልፈጽም እንጂ ለመሻር አልመጣሁም።

18፤ እውነት እላችኋለሁ፥ ሰማይና ምድር እስኪያልፍ ድረስ፥ ከሕግ አንዲት የውጣ ወይም አንዲት ነጥብ ከቶ አታልፍም፥ ሁሉ እስኪፈጸም ድረስ።

19፤ እንግዲህ ከነዚህ ከሁሉ ካነሱት ትእዛዛት አንዲቱን የሚሽር ለሰውም እንዲሁ የሚያስተምር ማንም ሰው በመንግሥተ ሰማያት ከሁሉ ታናሽ ይባላል፤ የሚያደርግ ግን የሚያስተምርም ማንም ቢሆን እርሱ በመንግሥተ ሰማያት ታላቅ ይባላል።

እየሱስ በዚህ አንቀጽ በግልጽ እንደሚነግረን ህግጋት አልተሻሩም:: ነገር ግን በሌላ ቦታ እንዲህ የሚል ቃል እናገኛለን።

"ሕጉ ምንም ፍጹም አላደረገምና፥ ስለዚህም የምትደክም የማትጠቅምም ስለሆነች የቀደመች ትእዛዝ ተሽራለች፥ ወደ እግዚአብሔርም የምንቀርብበት የሚሻል ተስፋ ገብቶአል። "

(ወደ ዕብራውያን 7: 18-19)

ጳውሎስ ደግሞ በዚህ አንቀጽ ህግ ፋይዳቢስ ስለሆነ እንደተሻረ ይገልጻል::

ጥያቄው፡- ህግ ተሽሯል ወይንስ አልተሸረም?

65. በክሱ ጽህፈት ላይ የተጻፈው ቃል ምንድን ነበር?

"ይህ **ኢየሱስ የአይሁድ ንጉሥ** ነው የሚል የክሱን ጽሕፈት ከራሱ በላይ አኖሩ። "

(የማቴዎስ ወንጌል 27: 37)

"የክሱ ጽሕፈትም። **የአይሁድ ንጉሥ** የሚል ተጽፎ ነበር። "

(የማርቆስ ወንጌል 15: 26)

"ይህ **የአይሁድ ንጉሥ ነው** ተብሎ በግሪክና በሮማይስጥ በዕብራይስጥም ፊደል የተጻፈ ጽሕፈት ደግሞ በእርሱ ላይ ነበረ። " (የሉቃስ ወንጌል 23: 38)

"ጲላጦስም ደግሞ ጽሕፈት ጽፎ በመስቀሉ ላይ አኖረው፤ ጽሕፈቱም። የአይሁድ ንጉሥ የናዝሬቱ ኢየሱስ የሚል ነበረ። " (የዮሐንስ ወንጌል 19: 19)

ጥያቄዉ፡-አንደሚታወቀው በክሱ ጽህፈት ላይ ሊጻፍ የሚችለው ቃል ከነዚህ መካከል አንዱ ነው፡፡ ታዲያ ከነዚህ ከአራቱ በክስ ጽህፈቱ ላይ በትክክል የተጻፈው የትኛው አገላለጽ ነው?

66. ሄሮድስ መጥምቁ ዮሀንስን መግደል ይፈልግ ነበርን?

"ሊገድለውም ወዶ ሳለ፥ **ሕዝቡ እንደ ነቢይ** ስለ አዩት ፈሩአቸው። " (የማቴዎስ ወንጌል 14: 5)

በዚህ አንቀጽ እንደምናየው ሄሮድስ መጥምቁ ዮሀንስን መግደል እርሱም እራሱ ይፈልግ እንደነበር ነው።።

ነገር ግን በሌላ ቦታ

(የማርቆስ ወንጌል 6)

19፤ ሄሮድያዳ ግን ተቃውማው ልትገድለው ትፈልግ ነበር አልቻለችም፤

20፤ ሄሮድስ ዮሐንስ ጻድቅና ቅዱስ ሰው እንደ ሆነ አውቆ ይፈራውና ይጠባበቀው ነበር፤ እርሱንም ሰምቶ በብዙ ነገር ያመነታ ነበር፤

በዚህ አንቀጽ ደግሞ የምናየው መግደል ትፈልግ የነበረ ሚስቱ ሄሮድያዳ እንጅ እርሱ አይደለም መግደል ሊፈልግ ይቅርና በቅዱስነቱ አስቦት ይፈራው ጭምር እንደነበር ነው።።

ጥያቄው፡- ሄሮድስ መጥምቁ ዮሀንስን መግደል ይፈልግ ነበር ወይንስ አይፈልግም?

<u>67. አስረኛው ማነው?</u>

<u>ከአስራ ሁለቱ የእየሱስ ደቀመዛሙርት ስም ዝርዝር ውስጥ አስረኛው ማነው?</u>

(የማርቆስ ወንጌል 3)

15፤ ድውዮችንም ሊፈውሱ አጋንንትንም ሊያወጡ ሥልጣን ይሆንላቸው ዘንድ አሥራ ሁለት አደረገ፤

16፤ ስምዖንንም ጴጥሮስ ብሎ ሰየመው፤

17፤ የዘብዴዎስንም ልጅ ያዕቆብን የያዕቆብንም ወንድም ዮሐንስን ቦአኔርጌስ ብሎ ሰየማቸው፥ የነጎድጓድ ልጆች ማለት ነው፤

18፤ እንድርያስንም ፊልጶስንም በርተሎሜዎስንም ማቴዎስንም ቶማስንም የእልፍዮስን ልጅ ያዕቆብንም **ታዴዎስንም** ቀነናዊውንም ስምዖንን፥

19፤ አሳልፎ የሰጠውንም የአስቆሮቱን ይሁዳን።

በተመሳሳይ ማቴወስ 10፡1-4 መመልከት ይቻላል

በነኝህ አንቀጾች እንደምንረዳው ከአስራ ሁለቱ ውስጥ አስረኛው ታዴዎስ እንደሆነ ነው፡፡ ነገር ግን በሌላ ቦታ እንዲህ የሚል ቃል እናገኛለን፡፡

(የሉቃስ ወንጌል 6)

13፤ በነጋም ጊዜ ደቀ መዛሙርቱን ጠራ፥ ከእነርሱም አሥራ ሁለት መረጠ ደግሞም ሐዋርያት ብሎ ሰየማቸው፤

14፤ እነርሱም፥ ጴጥሮስ ብሎ እንደ ገና የሰየመው ስምዖን፥ ወንድሙም እንድርያስ፥ ያዕቆብም ዮሐንስም፥ ፊልጶስም በርተሎሜዎስም፥

15፤ ማቴዎስም ቶማስም፥ የእልፍዮስ ልጅ ያዕቆብም ቀናተኛ የሚባለው ስምዖንም፥

16፤ የያዕቆብ ይሁዳም፥ አሳልፎ የሰጠውም የአስቆሮቱ ይሁዳ ናቸው።

በዚህ አንቀጽ ደግሞ ከነ ጭራሹ ታዴዎስ አልተጠቀሰም በርሱ ፈንታ የተጠቀሰው **የእልፍዮስ ልጅ ያዕቆብ** ነው።

ጥያቄ፦ የእየሱስ አስረኛ ደቀ-መዝሙር ታዴዎስ ነው ወይንስ የእልፍዮስ ልጅ ያዕቆብ

68. የተከተለው ሰው ማነው?

እየሱስ በታክስ መቅረጫው ቦታ አንድ ሰው አይቶ በነበረበት ወቅት ተከተለኝ ብሎታል የዚህ ሰው ስም ማነው?

"ከዚህም በኋላ ወጥቶ **ሌዊ** የሚባል ቀራጭ በመቅረጫው ተቀምጦ ተመለከተና። ተከተለኝ አለው። " (የሉቃስ ወንጌል 5: 27)

በተመሳሳይ ማርቆስ 2፡14 መመልከት ይቻላል

ከዚህ አንቀጽ የምንረዳው በቀረጥ መቅረጫው ላይ ተቀምጦ የነበረው ሰው ስሙ ሌዊ እንደሚባል ነው፡፡ ነገር ግን በሌላ ቦታ እንዲህ ይላል፦

"ኢየሱስም ከዚያ አልፎ በመቅረጫው ተቀምጦ የነበረ **ማቴዎስ** የሚባል አንድ ሰው አየና። ተከተለኝ አለው። ተነሥቶም ተከተለው። " (የማቴዎስ ወንጌል 9: 9)

በዚህ አንቀጽ የምንረዳው ደግሞ ሰውየው ስሙ ማቴወስ ይባል እንደነበር ነው፡፡

ጥያቄው፡- የቀራጩ ስም ሌዊ ነው ወይንስ ማቴወስ? የሚል ነው

69. እየሱስ የተሰቀለው ከፋሲካ ማዘጋጀት በፊት ነው ወይንስ በኋላ?

(የማርቆስ ወንጌል 14)

12፤ ፋሲካን በሚያርዱበት በቂጣ በዓል መጀመሪያ ቀን ደቀ መዛሙርቱ። ፋሲካን ትበላ ዘንድ ወዴት ሄደን ልናሰናዳ ትወዳለህ? አሉት።

13፤ ከደቀ መዛሙርቱም ሁለት ላከ እንዲህም አላቸው። ወደ ከተማ ሂዱ፥ ማድጋ ውኃ የተሸከመ ሰውም ይገናኛችኋል፤

14፤ ተከተሉት፥ የሚገባበትንም የቤቱን ጌታ። መምህሩ። ከደቀ መዛሙርቴ ጋር ፋሲካን የምበላበት የእንግዳ ቤት ወዴት ነው? ይላል በሉት።

15፤ እርሱም በደርብ ላይ ያለውን የተሰናዳና የተነጠፈ ታላቅ አዳራሽ ያሳያችኋል፤

16፤ በዚያም አሰናዱልን። ደቀ መዛሙርቱም ወጡ ወደ ከተማም ሄደው እንዳላቸው አገኙ፥ ፋሲካንም አሰናዱ።

17፤ በመሸም ጊዜ ከአሥራ ሁለቱ ጋር መጣ።

18፤ ተቀምጠውም ሲበሉ ኢየሱስ። እውነት

እላችኋለሁ፥ ከእናንተ አንዱ፥ እርሱም ከእኔ ጋር የሚበላው አሳልፎ ይሰጠኛል አለ።

ይህ አንቀጽ በግልጽ እንደሚነግረን እየሱስ የተሰቀለው የፈሲካ ዝግጅት ማዕድ በምሽት ከበላ በኋላ ነው፡፡ ነገር ግን በሌላ ቦታ እንዲህ ይላል፡፡

"ለፋሲካም የማዘጋጀት ቀን ነበረ፤ ስድስት ሰዓትም የሚያህል ነበረ፤ አይሁድንም። እነሆ ንጉሣችሁ አላቸው። "

(የዮሐንስ ወንጌል 19: 14)

በዚህ አንቀጽ ደግሞ የሚነግረን እየሱስ ተይዞ ለፍርድ የቀረበው ገና ለፋሲካ ዝግጅት ወቅት ቀን ላይ ነበር፡፡

ጥያቄው፡- እየሱስ የተሰቀለው ከፋሲካ ማዘጋጀት በፊት ነው ወይንስ በኋላ

70. ስቅለቱ እንዲቀርለት እየሱስ ለአባቱ ጸልዮ ነበርን?

(የሉቃስ ወንጌል 22)

41፤ ከእነርሱም የድንጋይ ውርወራ የሚያህል ራቀ፥ ተንበርክኮም። አባት ሆይ፥

42፤ **ብትፈቅድ ይህችን ጽዋ ከእኔ ውሰድ፤** ነገር ግን የእኔ ፈቃድ አይሁን የአንተ እንጂ እያለ ይጸልይ ነበር።

በተመሳሳይ ማቴወስ 26፡39 ማርቆስ 14፡36 እንደጸለየ ይገልጻሉ።

ነገር ግን በሌላ ቦታ ይህንን እናገኛለን፡፡

"፤ **አሁን ነፍሴ ታውካለች ምንስ እላለሁ? አባት ሆይ፥ ከዚህ ሰዓት አድነኝ።** ነገር ግን ስለዚህ ወደዚህ ሰዓት *መጣሁ።* "

(የዮሐንስ ወንጌል 12: 27)

በዚህ አንቀጽ ደግሞ እየሱስ ሁኔታው ቢያስጨንቀውም የመጣበትን አላማ አምኖ መቀበሉን ያሳያል፡፡

ጥያቄው፡- እየሱስ ስቅለቱ እንዲቀርለት አባቱን ተማጽኖ ነበር ወይንስ ውሳኔውን በጸጋ መቀበልን ብቻ መርጦ ነበር?

<u>7ነ. ጊዜው ምን ያክል ነው?</u>

አንደ ወንጌላት አገላለጽ እየሱስ ስቅለቱ እንዲቀርለት አባቱን ተማጽኗል፡፡ ታዲያ ለዚህ ጸሎት እየሱስ ከደቀመዛሙርቱ የተለየው ለምን ያህል ጊዜ ነው?

(የማቴዎስ ወንጌል 26)

36፤ በዚያን ጊዜ ኢየሱስ ከእነርሱ *ጋር* ጌቴሴማኒ ወደምትባል ስፍራ *መጣ* ደቀ መዛሙርቱንም። ወዲያ ሄጀ ስጸልይ ሳለ በዚህ ተቀመጡ አላቸው።

37፤ ጴጥሮስንም ሁለቱንም የዘብዴዎስን ልጆች ወስዶ ሊያዝን ሊተክዝም ጀመር።

38፤ ነፍሴ እስከ ሞት ድረስ እጅግ አዘነች፤ በዚህ ቆዩ ከእኔም ጋር ትጉ አላቸው።

39፤ ጥቂትም ወደ ፊት እልፍ ብሎ በፊቱ ወደቀና ሲጸልይ። አባቴ፥ ቢቻልስ፥ ይህች ጽዋ ከእኔ ትለፍ፤ ነገር ግን አንተ እንደምትወድ ይሁን እንጂ እኔ እንደምወድ አይሁን አለ።

40፤ ወደ ደቀ መዛሙርቱም መጣ፤ ተኝተውም አገኛቸውና ጴጥሮስን። እንዲሁም ከእኔ ጋር አንዲት ሰዓት እንኳ ልትተጉ አልቻላችሁምን?

41፤ ወደ ፈተና እንዳትገቡ ትጉና ጸልዩ፤ መንፈስስ ተዘጋጅታለች ሥጋ ግን ደካማ ነው አለው።

42፤ ደግሞ ሁለተኛ ሄዶ ጸለየና። አባቴ፥ ይህች ጽዋ ሳልጠጣት ታልፍ ዘንድ የማይቻል እንደ ሆነ፥ ፈቃድህ ትሁን አለ።

43፤ ደግሞም መጥቶ ዓይኖቻቸው በእንቅልፍ ከብደው ነበርና ተኝተው አገኛቸው።

44፤ ደግሞም ትቶአቸው ሄደ፥ ሦስተኛም ያንኑ ቃል ደግሞ ጸለየ።

45፤ ከዚያ ወዲያ ወደ ደቀ መዛሙርቱ መጥቶ። እንግዲህስ ተኙ ዕረፉም፤ እነሆ፥ ሰዓቲቱ ቀርባለች የሰው ልጅም በኃጢአተኞች እጅ አልፎ ይሰጣል።

46፤ ተነሡ፥ እንሂድ፤ እነሆ፥ አሳልፎ የሚሰጠኝ ቀርቦአል አላቸው።

ተመሳሳይ ማርቆስ 14፡32-42 መመልከት ይቻላል

በዚህ አንቀጽ እንደምንመለከተው ከእነሱ እየተለየ የጸለየው ለሶስት ጊዜ ነው፡፡ ነገር ግን በሌላ ቦታ ላይ እንዲህ ይላል፡፡

(የሉቃስ ወንጌል 22)

39፤ ወጥቶም እንደ ልማዱ ወደ ደብረ ዘይት ሄደ፤ ደቀ መዛሙርቱም ደግሞ ተከተሉት።

40፤ ወደ ስፍራውም ደርሶ። ወደ ፈተና እንዳትገቡ ጸልዩ አላቸው።

41፤ ከእነርሱም የድንጋይ ውርወራ የሚያህል ራቀ፥ ተንበርክኮም። አባት ሆይ፥

42፤ ብትፈቅድ ይህችን ጽዋ ከእኔ ውሰድ፤ ነገር ግን የእኔ ፈቃድ አይሁን የአንተ እንጂ እያለ ይጸልይ ነበር።

43፤ ከሰማይም መጥቶ የሚያበረታ መልአክ ታየው።

44፤ በፍርሃትም ሲጣጣር አጽንቶ ይጸልይ ነበር፤ ወዙም በምድር ላይ እንደሚወርድ እንደ ደም ነጠብጣብ ነበረ።

45፤ ከጸሎትም ተነሥቶ ወደ ደቀ መዛሙርቱ መጣና ከኀዘን የተነሣ ተኝተው ሲያገኛቸው።

46፤ ስለ ምን ትተኛላችሁ? ወደ ፈተና እንዳትገቡ ተነሥታችሁ ጸልዩ አላቸው።

በዚህ አንቀጽ ደግሞ እየሱስ የጸለየው ለአንድ ጊዜ ብቻ አንደሆነ ነው፡፡ በማርቆስና ማቴወስ ላይ የምንመለከተው ተመልሶ ለጸሎት የመሄዱ ጉዳይ ሉቃስ ላይ የለም፡፡

ጥያቄው፡- ከሁለቱ የትኛው ነው ዘገባ ነው ትክክል?

<u>72. በጸሎቱ ምን አለ?</u>

ማቴወስና ማርቆስ ሁለቶችም እየሱስ ለሶስት ጊዜያት መጸለዩን ዘግበዋል፡፡ታዲያ በሁለተኛው የጸሎት ጊዜ ምንድን ነበር ያለው?

"ደግሞም ሄዶ **ያንኑ ቃል** ጸለየ። " (የማርቆስ ወንጌል 14: 39)

በማርቆስ ገለጻ መሰረት እየሱስ ለሁለተኛ ጊዜ የጸለየው ያንኑ ቃል በድጋሜ ነው፡፡ ነገር ግን ወደ ማቴወስ ስንመለከት ግን ይህን እናገኛለን

"ደግሞ ሁለተኛ ሄዶ ጸለየና። **አባቴ፥ ይህች ጽዋ ሳልጠጣት ታልፍ ዘንድ የማይቻል እንደ ሆነ፥ ፈቃድህ ትሁን አለ።** " (የማቴዎስ ወንጌል 26: 42)

ጥያቄው፡- ማርቆስ እንዳለው ቃሉ ያንኑ ነው ወይንስ እንደማቴወስ የተለየ ቃል ነው?

73. መቶ አለቃው እየሱስ በሞተ ጊዜ ምንድን ነበር ያለው?

"በዚያም በአንጻሩ የቆመ የመቶ አለቃ እንደዚህ ጮኾ ነፍሱን እንደ ሰጠ ባየ **ጊዜ። ይህ ሰው በእውነት የእግዚአብሔር ልጅ ነበረ አለ። "**

(የማርቆስ ወንጌል 15: 39)

በማርቆስ አገላለጽ መሰረት መቶ አለቃው የተናገረው ቃል የእግዚአብሄር ልጅ እንደሆነ ነው። ከዚህ በተለየ ደግሞ ሉቃስ እንዲህ ይለናል።

"የመቶ አለቃውም የሆነውን ነገር ባየ ጊዜ። **ይህ ሰው በእውነት ጻድቅ ነበረ ብሎ እግዚአብሔርን አከበረ።** " (የሉቃስ ወንጌል 23: 47)

ጥያቄው፡- መቶ አለቃው የተጠቀመው ቃል የእግዚአብሄር ልጅ የሚለውን ወይስ ጻድቅ ነበር የሚለውን ነው?

74. እንደ ወንጌላት አገላለጽ እየሱስ ከመሞቱ በፊት መጨረሻ ያለው ቃል ምንድን ነው?

"ኢየሱስም በታላቅ ድምፅ ጮኾ። **አባት ሆይ፥ ነፍሴን በእጅህ አደራ እሰጣለሁ** አለ። ይህንም ብሎ ነፍሱን ሰጠ። "

(የሉቃስ ወንጌል 23: 46)

በዚህ አገላለጽ መሰረት የእየሱስ የመጨረሻ ንግግር አባት ሆይ ነፍሴን በእጅህ አደራ እሰጣለሁ የሚል ነበር፡፡ እስኪ የሀንስ ደግሞ ምን እንደሚል እንመልከት፡፡

"ኢየሱስም ሆምጣጤውን ከተቀበለ በኋላ። **ተፈጸመ** አለ፥ ራሱንም አዘንብሎ ነፍሱን አሳልፎ ሰጠ።" (የዮሐንስ ወንጌል 19: 30)

በዚህ አንቀጽ ደግሞ እየሱስ መጨረሻ ያለው ቃል "ተፈጸመ" የሚል ነው፡፡

ጥያቄው፡- እየሱስ ከመሞቱ ቀደም ብሎ መጨረሻ የተናገረው ቃል በትክክል ምንድን ነበር?

75. መቶ አለቃው እራሱ ነው የመጣው ወይንስ ሰዎችን ነው የላከው?

(የሉቃስ ወንጌል 7)

2፤ አንድ የመቶ አለቃም ነበረ፤ የሚወደውም ባሪያው ታሞ ሊሞት ቀርቦ ነበር።

3፤ ስለ ኢየሱስም በሰማ ጊዜ የአይሁድን ሽማግሌዎች ወደ እርሱ ላከና መጥቶ ባሪያውን እንዲያድን ለመነው።

4፤ እነርሱም ወደ ኢየሱስ መጥተው። ይህን ልታደርግለት ይገባዋል፤

5፤ ሕዝባችንን ይወዳልና ምኵራብም ራሱ ሠርቶልናል ብለው አጽንተው ለመኑት።

በዚህ አንቀጽ እንደምንረዳው መቶ አለቃው የአይሁድ ሽማግሌዎችን በመላክ እንዳስለመነው ነው። በሌላ ቦታ ደግሞ እንዲህ ይላል።

(የማቴዎስ ወንጌል 8)

5፤ ወደ ቅፍርናሆምም በገባ ጊዜ የመቶ አለቃ ወደ እርሱ ቀርቦ። ጌታ ሆይ፥

6፤ ብላቴናዬ ሽባ ሆኖ እጅግ እየተሣቀየ በቤት ተኝቶአል ብሎ ለመነው።

በዚህ አንቀጽ ደግሞ እራሱ መቶ አለቃው መጥቶ እንደለመነው ይገልጻል።

ጥያቄው፡- መቶ አለቃው ለመለመን ሽማግሌዎችን ነው የላከው ወይንስ እራሱ ነው የመጣው?

76. አዳም የተከለከለውን ዛፍ የበላ ቀን ሙቷል ወይንስ አልሞተም?

"ነገር ግን መልካምንና ክፉን ከሚያስታውቀው ዛፍ አትብላ፤ ከእርሱ በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህና። " (ኦሪት ዘፍጥረት 2: 17)

በዚህ አንቀጽ እንደሚነግረን አዳም አትብላ የተባለውን ዛፍ ከበላ የዛውን የበላ ቀን ይሞታል። በሌላ ቦታ ደግሞ እንዲህ ይለናል።

"አዳምም የኖረበት ዘመን ሁሉ ዘጠኝ መቶ ሠላሳ ዓመት ሆነ፤ ሞተም። " (ኦሪት ዘፍጥረት 5: 5)

ይህ አንቀጽ እንደሚነግረን ደግሞ አዳም ዛፉን ከበላ በኋላ አይደለም ወዲያውኑ ሊሞት ይቅርና ከዛም አልፎ ልጆቹን ወልዶ በአጠቃላይ ዘጠኝ መቶ ሰላሳ አመት እንደኖረ ነው::

ጥያቄው:- አዳም እንደተባለው የዛውን ቀን ሞቷል ወይንስ አልሞተም::

77. የሰው ልጅ የእድሜ ገደብ ስንት ነው?

"እግዚአብሔርም። መንፈሴ በሰው ላይ ለዘላለም አይኖርም፥ እርሱ ሥጋ ነውና፤ ዘመኖቹም **መቶ ሀያ ዓመት ይሆናሉ** አለ። " (ኦሪት ዘፍጥረት 6: 3)

ይህ አንቀጽ የሰው ልጅ የእድሜ ገደብ 120 አመት እንደሆነ ይነግረናል::

በሌላ አንቀጽ ደግሞ ከመቶ ሀያ አመት እድሜ በላይ የኖሩ ሰዎችን መልሶ ይጠቅስልናል:: ለአብነትም

ሴምም አርፋክስድን ከወለደ በኋላ አምስት መቶ ዓመት ኖረ፥ ወንዶችንም ሴቶችንም ወለደ፤ ሞተም። አርፋክስድም መቶ ሠላሳ አምስት ዓመት ኖረ፥ ቃይንምንም ወለደ፤ አርፋክስድም ቃይንምን ከወለደ በኋላ አራት መቶ ዓመት ኖረ፥ ወንዶችንም ሴቶችንም ወለደ፤ ሞተም። ቃይንምም መቶ ሠላሳ ዓመት ኖረ፥ ሳላንም ወለደ፤ ቃይንምም ሳላን ከወለደ በኋላ

ሶስት መቶ ሠላሳ ዓመት ኖረ፥ ወንዶችንም ሴቶችንም ወለደ፤ ሞተም። ኦሪት ዘፍጥረት 11:11-12

ሌሎችም ተመሳሳይ ብዙ አንቀጾችን መጥቀስ ይቻላል።

ጥያቄው፡ የሰው ልጅ የእድሜ ገደብ 120 ነው ወይንስ ከዚያ በላይ ነው?

78. ከእየሱስ ውጭ ወደ ሰማይ የወጣ አለ?

"ከሰማይም ከወረደ በቀር **ወደ ሰማይ የወጣ ማንም የለም**፥ እርሱም በሰማይ የሚኖረው የሰው ልጅ ነው። " (የዮሐንስ ወንጌል 3: 13)

በዚህ አንቀጽ መሰረት ወደ ሰማይ የወጣ ማንም የለም። ነገሮ ግን በሌላ ቦታ ግን እንዲህ የሚል ቃል እናነኛለን።

"ሲሄዱም። እያዘገሙም ሲጫወቱ፥ እነሆ፥ የእሳት ሰረገላና የእሳት ፈረሶች በመካከላቸው ገብተው ከፈሉአቸው፤ **ኤልያስም በዐውሎ ነፋስ ወደ ሰማይ ወጣ።**" (መጽሐፈ ነገሥት ካልዕ 2: 11)

ጥያቄው፡- ወደ ሰማይ የወጣ አለ ወይንስ የለም?

79. በስርዐት ተከፍኗል ወይንስ አልተከፈነም?

እየሱስ እንደ አይሁድ አገናነዝ ልማድ በስርዐት ተከፍኗል ወይንስ አልተከፈነም?

(የዮሐንስ ወንጌል 19)

39፤ ደግሞም አስቀድሞ በሌሊት ወደ ኢየሱስ መጥቶ የነበረ ኒቆዲሞስ መቶ ንጥር የሚያህል የከርቤና የእሬት ቅልቅል ይዞ መጣ።

40፤ የኢየሱስንም ሥጋ ወስደው እንደ አይሁድ አገናነዝ ልማድ ከሽቱ ጋር በተልባ እግር ልብስ ከፈኑት።

በዚህ አንቀጽ እንደምንመለከተው ኒቆዲሞስ የእየሡስን አካል በስርዐት እንደከፈነው ነው።።

ነገር ግን በሌላ ቦታ አንዲህ ይላል፦

"ሰንበትም ካለፈ በኋላ መግደላዊት ማርያም የያዕቆብም እናት ማርያም ሰሎሜም መጥተው ሊቀቡት ሽቱ ገዙ። " (የማርቆስ ወንጌል 16: 1)

በዚህ አንቀጽ ደግሞ የእየሱስን አካል ሽቶ ሊቀቡ እንደመጡ ይገልጻል።።

ጥያቄው፦ የእየሱስ አካል ተከፍኗል ወይንስ ሽቶ መቀባት የሚቻል አይነት ያልተከፈነ ነበር?

80. ሴቶቹስ ሽቶውን መቼ ነው የገዙት?

"ሰንበትም ካለፈ በኋላ መግደላዊት ማርያም የያዕቆብም እናት ማርያም ሰሎሜም መጥተው ሊቀቡት ሽቱ ገዙ። " (የማርቆስ ወንጌል 16: 1)

በዚህ አንቀጽ እንደተገለጸው ሽቶውን የገዙት ሰንበት ካለፈ በኋላ ነው።።

ነገር ግን ሌላ ቦታ ላይ እንዲህ ይላል፡፡

ከገሊላም ከእርሱ ጋር የመጡት ሴቶች ተከትለው መቃብሩን ሥጋውንም እንዴት እንዳኖሩት አዩ። ተመልሰውም ሽቱና ቅባት አዘጋጁ። **በሰንበትም እንደ ትእዛዙ ዐረፉ።**(የሉቃስ ወንጌል 23፥55-56)

ተጨማሪ

"ነገር ግን ከሳምንቱ በመጀመሪያው ቀን ያዘጋጁትን ሽቱ ይዘው ከእነርሱም ጋር አንዳንዶቹ ወደ መቃብሩ እጅግ ማልደው መጡ። " (የሉቃስ ወንጌል 24: ነ)

ይህ አንቀጽ ደግሞ ሽቶው ከሰንበት በኋላ የተገዛ ሳይሆን የሰንበት ቀን ጭምር ሽቶው አብሩዋቸው እንደነበር ይገልጻል፡፡ ይህ ማለት ሽቶው የተገዛው ከሰንበት በፊት ነው።

ጥያቄ፦ ሽቶው ከሰንበት በኋላ የተገዛ ነው ወይንስ የሰንበት ቀንም አብሯቸው ነበር?

8ነ. ሴቶቹ ወደ መቃብሩ የመጡት ለምንድን ነበር?

"በሰንበትም መጨረሻ መጀመሪያው ቀን ሲነጋ መግደላዊት ማርያምና ሁለተኛይቱ ማርያም **መቃብሩን ሊያዩ መጡ።** " (የማቴዎስ ወንጌል 28: ነ)

በዚህ አንቀጽ በግልጽ እንደተነገረን የመጡበት አላማ መቃብሩን ማየት ነበር፡፡ስለ ሽቶም ሆነ ሌላ ነገር የተገለጸ ነገር የለም፡፡

ተጨማሪ

"ከገሊላም ከእርሱ ጋር የመጡት ሴቶች ተከትለው መቃብሩን **ሥጋውንም እንዴት እንዳኖሩት አዩ።**" (የሉቃስ ወንጌል 23: 55)

በሌላ ቦታ ደግሞ

"ሰንበትም ካለፈ በኋላ መግደላዊት ማርያም የያዕቆብም እናት ማርያም ሰሎሜም መጥተው **ሊቀቡት ሽቱ ገዙ።** " (የማርቆስ ወንጌል 16: 1)

ይህ አንቀጽ ደግሞ ሽቶ አንደያዙና ሊቀቡት አንደመጡ ይነግረናል፡፡በሌላ ቦታ ደግሞ

"ከሳምንቱም በፊተኛው ቀን መግደላዊት ማርያም ገና ጨለማ ሳለ ማለዳ ወደ መቃብር መጣች ድንጋዩም ከመቃብሩ ተፈንቅሎ አየች። " (የዮሐንስ ወንጌል 20: 1)

ዮሀንስ ደግሞ ከነ ጭራሹ የመጣችበትን አላማም አይገልጽም፡፡

ጥያቄው፡- በትክክል ሴቶቹ ለምን አላማ ብለው ነበር የመጡት?

82. ሴቶቹ ወደ መቃብር የመጡት መቼ ነው?

"ከሳምንቱም በፊተኛው ቀን መግደላዊት ማርያም **ገና ጨለማ ሳለ ማለዳ** ወደ መቃብር መጣች ድንጋዩም ከመቃብሩ ተፈንቅሎ አየች። " (የዮሐንስ ወንጌል 20: 1)

በዚህ አንቀጽ እንደተገለፀው መግደላዊት ማርያም ስትመጣ ገና ጨለማ ነበር፡፡ ነገር ግን በሌላ ቦታ እንዲህ ይላል፡፡

"ከሳምንቱም በፊተኛው ቀን እጅግ በማለዳ **ፀሐይ ከወጣ በኋላ** ወደ መቃብር መጡ። " (የማርቆስ ወንጌል 16: 2)

ይህ አንቀጽ ደግሞ እንደሚነግረን የመጡት ጸሀይ ከወጣ በኋላ እንደሆነ ነው፡፡

ጥያቄው፡- ሴቶቹ የመጡት ጸሀይ ከወጣ በኋላ ነው ወይንስ ገና ጨለማ ሳለ?

83. ወደ መቃብሩ ሲመጡ ስንት ነበሩ?

"ከሳምንቱም በፊተኛው ቀን **መግደላዊት ማርያም** ገና ጨለማ ሳለ ማለዳ ወደ መቃብር መጣች ድንጋዩም ከመቃብሩ ተፈንቅሎ አየች። " (የዮሐንስ ወንጌል 20: 1)

በዚህ አንቀጽ እንደተገለጸው ወደ መቃብሩ የመጣችው መግደላዊት ማርያም ብቻ አንደሆነች ነው፡፡ በሌላ ቦታ ደግሞ

"በሰንበትም መጨረሻ መጀመሪያው ቀን ሲነጋ **መግደላዊት ማርያምና ሁለተኛይቱ ማርያም** መቃብሩን ሊያዩ መጡ። " (የማቴዎስ ወንጌል 28: 1)

እዚህ ጋ ደግሞ የመጡት ሰዎች ሁለት እንደሆኑ ተገልጿል፡፡ ነገር ግን ሌላ ቦታ ደግሞ

"ሰንበትም ካለፈ በኋላ መግደላዊት ማርያም የያዕቆብም እናት ማርያም ሰሎሜም መጥተው ሊቀቡት ሽቱ ገዙ። " (የማርቆስ ወንጌል 16: 1)

እዚህ ጋ ደግሞ የመጡት ሰዎች ብዛት ሶስት እንደሆኑ ተገልጽዋል።

ጥያቄው፦ ሴቶቹ ወደ መቃብሩ ሲመጡ ስንት ነበሩ?

84. ቋጥኙ የት ነበር?

በመቃብሩ ደጃፍ ትልቅ ቋጥኝ ነበር፤ ይህ በሩን የዘጋው ትልቅ ቋጥኝ ሴቶቹ ከቦታው ሲደርሱ የት ነበር?

"ድንጋዩ እጅግ ትልቅ ነበርና፤ አሻቅበውም አይተው ድንጋዩ ተንከባሎ እንደ ነበር ተመለከቱ። " (የማርቆስ ወንጌል 16: 4)

በዚህ አንቀጽ እንደተገለጸው እነሱ ሲደርሱ ድንጋዩ ተንከባሎ ነበር።

ሌላ ቦታ በተመሳሳይ እንዲህ ይላል

"ድንጋዩንም ከመቃብሩ ተንከባሎ አገኙት፥ " (የሉቃስ ወንጌል 24: 2)

ሌላ ተጨማሪ ዮሀንስ 20፡1 እንዲህ ይነበባል

"ከሳምንቱም በፊተኛው ቀን መግደላዊት ማርያም ገና ጨለማ ሳለ ማለዳ ወደ መቃብር መጣች ድንጋዩም ከመቃብሩ ተፈንቅሎ አየች። " (የዮሐንስ ወንጌል 20: 1)

ሶስቱ አንቀጾች በተመሳሳይ አገላለጽ እንደሚነግሩን ሲደርሱ ድንጋዩ ተንከባሎ እንዳገኙት ይገልጻል። ነገር ግን ማቴወስ ከዚህ የተለየ ነገር ይለናል

በሰንበትም መጨረሻ መጀመሪያው ቀን ሲነጋ መግደላዊት ማርያምና ሁለተኛይቱ ማርያም መቃብሩን ሊያዩ መጡ። እነሆም፥ የጌታ መልአክ ከሰማይ ስለ ወረደ ታላቅ የምድር መናወጥ ሆነ፤ ቀርቦም ድንጋዩን አንከባሎ በላዩ ተቀመጠ።የማቴዎስ ወንጌል 28፥ 1-2

እንደ ማቴወስ አገላለጽ ደግሞ መጀመሪያውኑ ተንከባሎ ሳይሆን ያገኙት መላዕኩ ወርዶ ነው ያንከባለለው። እነሱም ሲያንከባልለው ሳይቀር ተመልክተዋል።

ጥያቄው፡- ድንጋዩ ተንከባሎ ነው የጠበቃቸው ወይንስ ከደረሱ በኋላ ነው መላዕኩ ያንከባለለው?

85. ለሴቶቹ በእየሱስ አካል ዙርያ የነገራቸው አካል ነበር?

"ፈጥናችሁም ሂዱና። ከሙታን ተነሣ፥ እነሆም፥ ወደ ገሊላ ይቀድማችኋል በዚያም ታዩታላችሁ ብላችሁ ለደቀ መዛሙርቱ ንገሩአቸው። " (የማቴዎስ ወንጌል 28: 7)

በተመሳሳይ

ወደ መቃብሩም ገብተው ነጭ ልብስ የተጎናጸፈ ጎልማሳ በቀኝ በኩል ተቀምጦ አዩና ደነገጡ። እርሱ ግን። አትደንግጡ፤ የተሰቀለውን የናዝሬቱን ኢየሱስን ትፈልጋላችሁ፤ ተነሥቶአል፥ በዚህ የለም፤ እነሆ እርሱን ያኖሩበት ስፍራ። ነገር ግን ሄዳችሁ ለደቀ መዛሙርቱ ለጴጥሮስም። ወደ ገሊላ ይቀድማችኋል፤ እንደ ነገራችሁ በዚያ ታዩታላችሁ ብላችሁ ንገሩአቸው አላቸው።

(የማርቆስ ወንጌል 16፥5-7 /ተጨማሪ ሉቃስ 24፡4 ሉቃስ 24፡23)

በነዚህ አንቀጾች አንደምንረዳው እየሱስ ከሙታን መነሳቱን አስመልከቶ ነጭ ልብስ የተጎናጸፈው ሰውየ እንዲሁም መላዕክት የተባሉት አካላት ነግረዋቸዋል።።

ነገር ግን ሌላ ቦታ እንዲህ እናገኛለን

"እየሮጠችም ወደ ስምዖን ጴጥሮስና ኢየሱስ ይወደው ወደ ነበረው ወደ ሌላው ደቀ መዝሙር መጥታ። ጌታን ከመቃብር ወስደውታል ወዴትም እንዳኖሩት አናውቅም አለቻቸው። " (የዮሐንስ ወንጌል 20: 2)

በዚህ አንቀጽ ደግሞ መግደላዊት ማርያም ጭራሽ ምንም እንደተከሰተ አንደማያውቁ ለደቀመዛሙርቱ ስትነግራቸው እናያለን።።

ጥያቄው፡- እየሱስ ከሙታን እንደተነሳ ተነግሯቸዋል ወይንስ ጭራሽ አያውቁም ነበር?

86. የትና በምን ሁኔታ?

መግደላዊት ማርያም ለመጀመሪያ ጊዜ እየሱስ ሞቶ ከተነሳ በኋላ ያገኘችው የት ነው? በምንስ ሁኔታ ነው የተገናኙት?

እነሆም፥ ነገርኋችሁ። በፍርሃትና በታላቅ ደስታም ፈጥነው ከመቃብር ሄዱ፥ ለደቀ መዛሙርቱም ሊያወሩ ሮጡ። እነሆም፥ ኢየሱስ አገኛቸውና። ደስ ይበላችሁ አላቸው። እነርሱም ቀርበው እግሩን ይዘው ሰገዱለት።

ማቴወስ 28፡8-9

በዚህ አንቀጽ እንደምንረዳው መግደላዊት ማርያም እየሱስን ለመጀመሪያ ጊዜ ያገኘችው ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ መቃብሩ በሄዱ ጊዜ ነው፡፡ አንቀጹን ከላይ ጀምሮ ማንበብ ይቻላል፡፡

ነገር ግን ሌላ ቦታ ላይ እንዲህ ይላል

ይህንም ብላ ወደ ኋላ ዘወር ስትል ኢየሱስን ቆሞ አየችው፤ ኢየሱስም እንደ ሆነ አላወቀችም። ኢየሱስም። አንቺ ሴት፥ ስለ ምን ታለቅሻለሽ? ማንንስ ትፈልጊያለሽ? አላት። እርስዋም የአትክልት ጠባቂ መስሎአት። ጌታ ሆይ፥ አንተ ወስደኸው እንደ ሆንህ ወዴት እንዳኖርኸው ንገረኝ እኔም እወስደዋለሁ አለችው። ኢየሱስም። ማርያም አላት። እርስዋ ዘወር ብላ በዕብራይስጥ። ረቡኒ አለችው፤ ትርጓሜውም። መምህር ሆይ ማለት ነው።

ዮሀንስ 20፡14-16

በዚህ አገላለጽ መሰረት ደግሞ መግደላዊት ማርያም እየሱስን ለመጀመሪያ ጊዜ ያገኘቸው መቃብሩን ለማየት ለሁለተኛ ጊዜ በሄደች ወቅት ነው።።

ጥያቄው፡- ማርያም መግደላዊት እየሱስ ጋር የተገናኘቸው የመጀመሪያ መቃብሩን ለማየት የሄደች ጊዜ ነው ወይንስ ለሁለተኛ ጊዜ በሄደችበት ወቅት ነው?

87. እየሱስ ለደቀመዛሙርቱ ያስተላለፈው መልዕክት ምንድን ነበር?

"በዚያን ጊዜ ኢየሱስ። አትፍሩ፤ ሄዳችሁ **ወደ ገሊላ እንዲሄዱ** ለወንድሞቼ ተናገሩ፥ በዚያም ያዩኛል አላቸው። " (የማቴዎስ ወንጌል 28: 10)

በዚህ አንቀጽ እንደተገለጸው እየሱስ እንዲነገር ለደቀመዛሙርቱ ያዘዛቸው ትዕዛዝ ወደ ገሊላ ሂዱ የሚል ነበር፡

በሌላ ቦታ ግን አንዲህ ይላል

"ኢየሱስም። ገና ወደ አባቴ አላረግሁምና አትንኪኝ፤ ነገር ግን ወደ ወንድሞቼ ሄደሽ። እኔ ወደ አባቴና ወደ አባታችሁ ወደ አምላኬና ወደ አምላካችሁ ዓርጋለሁ ብለሽ ንገሪአቸው አላት። " (የዮሐንስ ወንጌል 20: 17)

ጥያቄው፡- እየሱስ በትክክል ለደቀመዛሙርቱ ንገሪያቸው ያለው ትዕዛዝ ምንድን ነበር?

88. የምድያም ነጋዴዎች ዮሴፍን ለማን ነበር የሸጡት?

"የምድያም ነጋዶችም አለፉ፤ እነርሱም ዮሴፍን አንሥተው ከጕድጓድ አወጡት፤ **ለእስማኤላውያንም** ዮሴፍን በሀያ ብር ሸጡት፤ እነርሱም ዮሴፍን ወደ ግብፅ ወሰዱት። " (ኦሪት ዘፍጥረት 37: 28)

በዚህ አንቀጽ እንደምንረዳው የምድያን ነጋዴዎች ዮሴፍን የሸጡት ለእስማኤላውያን ነበር። ነገር ግን በሌ ቦታ ደግሞ እንዲህ የሚል እናገኛለን

"እነዚያ የምድያም ሰዎች ግን ዮሴፍን በግብፅ ለፈርዖን ጃንደረባ ለዘበኞቹ አለቃ ለጲጥፋራ ሸጡት። (ኦሪት ዘፍጥረት 37: 36)

ይህ አንቀጽ ደግሞ የሚነግረን የምድያም ሰዎች ዮሴፍን የሸጡት በግብጽ ለፈርዖን ጃንደረባ ለዘበኞዎቹ አለቃ ነው።

ጥያቄው፡- የየምድያም ነጋዴዎች ዮሴፍን ለማን ነበር የሸጡት?

89. ዮሴፍን ወደ ግብጽ ያመጣው ማን ነው?

"የምድያም ነጋዶችም አለፉ፤ እነርሱም ዮሴፍን አንሥተው ከጕድጓድ አወጡት፤ ለእስማኤላውያንም ዮሴፍን በሀያ ብር ሸጡት፤ እነርሱም ዮሴፍን ወደ ግብፅ ወሰዱት። " (ኦሪት ዘፍጥረት 37: 28)

በዚህ አንቀጽ እንደተገለጸው ዮሴፍን ወደ ግብጽ የወሰዱት እስማኤላውያን ናቸው።

ነገር ግን በሌላ ቦታ ደግሞ እንዲህ የሚል እናገኛለን

"እነዚያ የምድያም ሰዎች ግን ዮሴፍን በግብፅ ለፈርዖን ጃንደረባ ለዘበኞቹ አለቃ ለጲጥፋራ ሸጡት። (ኦሪት ዘፍጥረት 37: 36)

ይህ አንቀጽ ደግሞ በግብጽ ለፈርኦን ጃነደረባ የሸጡት የምድያም ሰዎች አንደሆኑ ይገልጻል። ለሶስተኛ ጊዜ ደግሞ ለየት ባለ መልኩ ሌላ ግጭት እራሱ ዬሴፍ እንዲህ ሲል ይደመጣል

"ዮሴፍም ወንድሞቹን። ወደ እኔ ቅረቡ አለ። ወደ እርሱም ቀረቡ። እንዲህም አላቸው። ወደ ግብፅ የሸጣችሁኝ እኔ ወንድማችሁ ዮሴፍ ነኝ። " (ኦሪት ዘፍጥረት 45: 4)

በዚህ አንቀጽ ደግሞ ዮሴፍን ወደ ግብጽ የሸጡት ወንድሞቹ እራሳቸው እንደሆኑ ይገልጻል።

ጥያቄው፡- እየሱስን ወደ ግብጽ የወሰዱት እነማን ናቸው?

90. አምላክ ይጸጸታል ወይንስ አይጸጸትም?

"የእስራኤል ኃይል እንደ ሰው **የሚጸጸት አይደለምና** አይዋሽም አይጸጸትምም አለው። " (መጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ 15: 29)

በዚህ አንቀጽ እንደምንረዳው እግዚአብሄር በባህሪው እንደማይጸጸት ነው። ሌላ ቦታ ግን እንዲህ ይላል

"፤ የእግዚአብሔርም ቃል። ሳኦል እኔ ከመከተል ተመልሶአልና፥ ትእዛዜንም አልፈጸመምና ስላነገሥሁት **ተጸጸትሁ** ብሎ ወደ ሳሙኤል መጣ። ሳሙኤልም ተቈጣ፤ ሌሊቱንም ሁሉ ወደ እግዚአብሔር ጮኸ። " (መጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ 15: 10፤11)

እግዚአብሄር እንደተጸጸተ የተገለጸባቸው ቦታዎች እነዚህ ብቻዎች አይደሉም፤ የትየለሌ ናቸው። ጥቂቶችን ሰጥቼ ልለፍ

"እግዚአብሔርም ሰውን በምድር ላይ በመፍጠሩ **ተጸጸተ**፥ በልቡም አዘነ። "

(ኦሪት ዘፍጥረት 6: 6)

"እግዚአብሔርም። የፈጠርሁትን ሰው ከምድር ላይ አጠፋለሁ፥ ከሰው እስከ እንስሳ እስከ ተንቀሳቃሽም እስከ ሰማይ ወፍም ድረስ፤ ስለ ፈጠርኋቸው ተጸጽቼአለሁና አለ። " (ኦሪት ዘፍጥረት 6: 7)

"ሳኦልም ወደ ቤቱ ወደ ጊብዓ ወጣ። ሳሙኤልም እስከ ሞተበት ቀን ድረስ ሳኦልን ለማየት ዳግመኛ አልሄደም፥ ሳሙኤልም ለሳኦል አለቀሰ፤ እግዚአብሔርም በእስራኤል ላይ ሳኦልን ስላነገሠ ተጸጸተ። (መጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ 15: 35)

"እግዚአብሔርም ስለዚህ ነገር ተጸጸተ፤ ይህ አይሆንም፥ ይላል እግዚአብሔር። " (ትንቢተ አሞጽ 7: 3)

ጥያቄው፡- አምላክ ይጸጸታል ወይንስ አይጸጸትም? የሚል ነው።።

91. የትኛውን ውሀ ቀየሩት?

"ሙሴና አሮንም እግዚአብሔር እንዳዘዛቸው እንዲሁ አደረጉ፤ በትሩንም አነሣ፥ በፈርዖንና በባሪያዎቹም ፊት የወንዙን ውኃ መታ፤ **የወንዙም ውኃ ሁሉ ተለውጦ ደም ሆነ።** " (ኦሪት ዘጸአት 7: 20)

በዚህ አንቀጽ እንደተገለጸው ሙሉ ለሙሉ የወንዝ ውሀው በተዐምር ወደ ደምነት ተለውጧል። **ልብ ይበሉ ውሀው ሁሉ ነው የተቀየረው።**

ነገር ግን አንቀጹ ትንሽ ወረድ ብሎ እንዲህ ይለናል።

"የግብፅም ጠንቋዮች በአስማታቸው **እንዲሁ** አደረጉ፤ እግዚአብሔርም እንደተናገረ የፈርዖን ልብ ጸና፥ አልሰማቸውምም። " (ኦሪት ዘጸአት 7: 22)

በዚህ አንቀጽ እንደምንረዳው ደግሞ የግብጽ ጠንቋዮችም ተመሳሳይ ነገር እንዳደረጉ ነው። ይህ ግን ጭራሽ የማይሆን ነገር ነው። ምክንያቱም መጀመሪያውኑ ሙሴና ወንድሙ ውሀውን በጠቅላላ ወደ ደምነት ከቀየሩት ጠንቋዮቹ **የትኛውን ውሀ ነው የቀየሩት**? ይህ አስተዋይ ያልሆነ ጸሀፊ የፈጸመው ግልጽ ግጭት ነው

ጥያቄው፦ ዉሃ ሙሉ በሙሉ ከተቀየረ ጠንቋዮቹ ዉሃ ከየት አመጡ?

92. ጎልያድን የገደለው ማን ነው?

"**ዳዊትም** ፍልስጥኤማዊውን በወንጭፍና በድንጋይ አሸነፈው፥ ፍልስጥኤማዊውንም መትቶ ገደለ፤ በዳዊትም እጅ ሰይፍ አልነበረም። " (መጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ 17: 50)

ሙሉ ታሪኩን ስንመለከት በዚህ አንቀጽ መሰረት ጎልያድን የገደለው ዳዊት ነበር። ነገር ግን በሌላ ቦታ እንዲህ የሚል እናገኛለን::

"ደግሞም በጎብ ላይ ከፍልስጥኤማውያን ጋር ሰልፍ ነበረ፤ የቤተ ልሔማዊውም የየዓሬኦርጊም ልጅ **ኤልያናን** የጦሩ የቦ እንደ ሸማኔ መጠቅለያ የነበረውን የጌት ሰው ጎልያድን ገደለ። " (መጽሐፈ ሳሙኤል ካልዕ 21: 19)

በዚህ አንቀጽ ደግሞ ጎልያድን ገደለ የተባለው ኤልያናን ነው::

ጥያቄው፡- ጎልያድን የገደለው ዳዊት ነው ወይንስ ኤልያናን?

93. ሳዖልን የገደለው ማን ነው?

"ሰልፍም በሳኦል ላይ ጠነከረ፥ ቀስተኞችም አገኙት፤ እርሱም ከቀስተኞቹ የተነሣ እጅግ ተጨነቀ። ሳኦልም ጋሻ ጃግሬውን። እነዚህ ቈላፋን መጥተው እንዳይወጉኝና እንዳይሳለቁብኝ ሰይፍህን መዝዘህ ውጋኝ አለው። ጋሻ ጃግሬው ግን እጅግ ፈርቶ ነበርና እንቢ አለ። ሳኦልም ሰይፉን ወስዶ በላዩ ወደቀ።" መጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ 31:3-5

በዚህ አንቀጽ እንደምንረዳው ሳኦል ማንም ሳይገድለው ሰይፉን ወስዶ በላዩ ላይ በመውደቅ መሞቱን ነው፡፡ ነገር ግን በሌላ ቦታ እንዲህ ይላል፡-

"እኔም ከወደቀ በኋላ አለ መዳኑን አይቼ በላዩ ቆሜ ገደልሁት፤ በራሱም ላይ የነበረውን ዘውድ በክንዱም የነበረውን ቢተዋ ወሰድሁ፥ ወደዚህም ወደ ጌታዬ አመጣሁት። " (መጽሐፈ ሳሙኤል ካልዕ ፡ 10)

በዚህ አንቀጽ ደግሞ እንደምረዳው የገደለው አማሌቃዊ ግለሰብ እንደሆነ ነው። በመግደሉ ምክንያትም ዳዊት ሰውየው ላይ ፈርዶበት እንደገደለው እዛው ምዕራፍ ላይ እንረዳለን።

ጥያቄው ፡-ሳኦል የሞተው ራሱን እጠፍቶ ነው? ወይንስ አማሌቃዊ ግለሰብ ነው የገደለው?

94. ሁሉም የሰው ልጅ ሀጥያት ይሰራል ወይስ አይሰራም?

«የማይበድልም ሰው የለምና....» ነኛ ነገስት 8፡46

በተመሳሳይ

ኃጢአት የለብንም ብንል ራሳችንን እናስታለን፥ እውነትም በእኛ ውስጥ የለም። በኃጢአታችን ብንናዘዝ ኃጢአታችንን ይቅር ሊለን ከዓመፃም ሁሉ ሊያነጻን የታመነና ጻድቅ ነው። ኃጢአትን አላደረግንም ብንል ሐሰተኛ እናደርገዋለን ቃሉም በእኛ ውስጥ የለም።

ነኛ ዮሀንስ ፡8-10

ተመሳሳይ አንቀጾች 2ኛ ቆሮንቶስ 6፡36 መፅሀፈ ምሳሌ 20፡9

ነገር ግን በተቃሪኒው በሌላ ቦታ ደግሞ እንዲህ የሚል እናገኛለን፡፡

"ስለዚህ የዲያብሎስን ሥራ እንዲያፈርስ የእግዚአብሔር ልጅ ተገለጠ። ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ ኃጢአትን አያደርግም፥ ዘሩ በእርሱ ይኖራልና፤ ከእግዚአብሔርም ተወልዶአልና ኃጢአትን ሊያደርግ አይችልም። " (1ኛ የዮሐንስ መልእክት 3: 9)

በዚህ አንቀጽ ደግሞ የእግዚአብሄር ልጆች ሀጥያት ሊያደርጉ አይችልም ሲል ይገልጻል፡፡

ጥያቄው፡- የሰው ልጅ በጠቅላላ ሀጥያት ይሰራል ወይንስ የማይሰሩ አሉ?

95. እያንዳንዱ የማንን ሸክም ይሸከም?

"ከእናንተ እያንዳንዱ የአንዱን ሸክም ይሸከም እንዲሁም የክርስቶስን ሕግ ፈጽሙ። " (ወደ ገላትያ ሰዎች 6: 2)

በዚህ አንቀጽ አንዱ የሌላውን ሸክም መሸከም እንደለበት ይገልጻል፡፡ በሌላ ቦታ ደግሞ እንዲህ ይላል

"እያንዳንዱ የገዛ ራሱን ሸክም ሊሸከም ነውና። " (ወደ ገላትያ ሰዎች 6: 5)

በዚህ አንቀጽ ደግሞ የሰው ልጅ እንዲሸከም የታዘዘው የራሱን ሸክም ነው።።

ጥያቄው፦ የሰው ልጅ የማንን ሸክም ነው የሚሸከመው?

96. እየሱስ ከትንሳኤ በኋላ ለስንት ደቀመዛሙርት ነው የታያቸው?

«ለኬፋም ታየ በኋላም **ለዐሥራ፡ኹለቱ፤**» 1ኛ ቆሮንቶስ 15፡5

በዚህ አንቀጽ የምንረዳው እየሱስ የታየው ለአስራሁለቱ ደቀመዛሙርት እንደሆነ ነው።። ነገር ግን ሌላ ቦታ ላይ በታቃራኒ ደግሞ እንዲህ የሚል እናገኛለን።።

አሥራ አንዱ ደቀ መዛሙርት ግን ኢየሱስ ወዳዘዛቸው ተራራ ወደ ገሊላ ሄዱ፥ ባዩትም ጊዜ ሰገዱለት፤ የተጠራጠሩ ግን ነበሩ።

የማቴዎስ ወንጌል 28፥16-17

በተጨማሪም ማቴወስ 27፡3-5፣ የሀዋርያት ስራ 1፡9-26፣ማርቆስ 16፡14፣ ሉቃስ 24፡9 እንዲሁም ሉቃስ 24፡3 መመልከት ይቻላል።።

በነኝህ አንቀጾች መሰረት ደግሞ እየሱስ የታየው **ለአስራ አንዱ** ነው።። ምክንያቱም እንደ ወንጌላት አገላለጽ አሳልፎ የሰጠው ይሁዳ አሳልፎ ከሰጠው በኋላ ወዲያውኑ በመጸጸት ብሩን መልሶ ታንቆ ሞቷልና ነው (ማቴዎስ 27፡3-6)

ጥያቄው፡- እየሱስ ከትንሳኤ በኃላ የታየው ለስንት ደቀመዛሙርት ነው?

97. እየሱስ ከተጠመቀ በኋላ በሶስተኛው ቀን የት ነበር?

«በአንተ ደስ ይለኛል የሚል ድምፅ ከሰማያት መጣ። ወዲያውም መንፈስ ወደ ምድረ በዳ አወጣው። በምድረ በዳም ከሰይጣን እየተፈተነ አርባ ቀን ሰነበተ ከአራዊትም ጋር ነበረ፥ መላእክቱም አገለገሉት።» ማርቆስ 1፡11-13

በዚህ አንቀጽ መሰረት እየሱስ ከተጠመቀ በኋላ ወዲያውኑ ወደ ምድረ በዳ ወጥቶ ለአርባ ቀን በሰይጣን እንደተፈተነ ይገልጻል፡

በሌላ ቦታ ደግሞ እንዲህ ይላል

«በነገው ደግሞ ዮሐንስ ከደቀ፡መዛሙርቱም ኹለት ቆመው ነበር፥» ዮሀንስ 1፡35

እንደ ዮሀንስ አገላለጽ በበነገታው ሁለት ደቀመዛሙርት ተከተሉት በሁለተኛው ቀን ደግሞ ከጥቂት ደቀመዛሙርቱ ጋር በመሆን ወደ ገሊላ ሄዷል

«በነገው ኢየሱስ ወደ ገሊላ ሊወጣ ወደደ፥ፊልጶስንም አገኘና፡-ተከተለኝ አለው።» ዮሀንስ 1፡44

በሶስተኛው ቀን ደግሞ ጣና ዘገሊላ ሰርግ ላይ ታድሞ ነበር።

በሦስተኛውም ቀን በገሊላ ቃና ሰርግ ነበረ፥ የኢየሱስም እናት በዚያ ነበረች፤ ኢየሱስም ደግሞ ደቀ መዛሙርቱም ወደ ሰርጉ ታደሙ።

ዮሀንስ 2፡1-2

ጥያቄው ፡- እየሱስ ከተጠመቀ በኃላ ባሉት ቀናት የት ነበር? በሰይጣን ሲፈተን ነበር ወይንስ ከላይ በተዘረዘሩት ቦታዎች ነበር?

98. ሄሮድስ እየሱስ በልጅነቱ ሳለ ነው የሞተው ወይንስ ከዚያ በኃላ ነው?

«ሄሮድስም ከሞተ በኋላ፥ እነሆ፥ የጌታ መልአክ በግብፅ ለዮሴፍ በሕልም ታይቶ። የሕፃኑን ነፍስ የፈለጉት ሞተዋልና ተነሣ፥ ሕፃኑን እናቱንም ይዘህ ወደ እስራኤል አገር ሂድ አለ። እርሱም ተነሥቶ ሕፃኑንና እናቱን ያዘና ወደ እስራኤል አገር ገባ። በአባቱም በሄሮድስ ፈንታ አርኬላዎስ በይሁዳ እንደ ነገሠ በሰማ ጊዜ፥ ወደዚያ መሄድን ፈራ፤ በሕልምም ተረድቶ ወደ ገሊላ አገር ሄደ፤ » ማቴዎስ 2፡19-22

በዚህ አገላለጽ መሰረት እየሱስ ከግብጽ ወደ እየሩሳሌም የሄደው ሄሮድስ ከሞተ በኋላ ነው፡፡ ይህም ሄሮድስ የሞተው እንደማቴወስ አገላለጽ እየሱስ ገና ልጅ በነበረበት ጊዜ ነው፡፡

ነገር ግን ሉቃስ ሌላ ተቃራኒ ታሪክ ይነግረናል፡፡

"የአሥራ ሁለት ዓመት ልጅ በሆነ ጊዜ፥ እንደ በዓሉ ሥርዓት ወደ ኢየሩሳሌም ወጡ፤ " (የሉቃስ ወንጌል 2: 42)

እንደ ሉቃስ አገላለጽ መሰረት ደግሞ እየሱስ ወደ ግብጽ ሄደ የሚለው ታሪክ በሱ ዘንድ ተቀባይየት የለውም፡፡ማርቆስ ይባስ ብሎም እየሱስ ከተጠመቀና ደቀመዛሙርት አፍርቶ ሳይቀር በልጅነቱ ሞቷል ተብሎ የነበረው ሄሮድስ በህይወት እንደ ነበር ይገልጻል፡፡ ለዛውም መጥመቁ ዮሀንስ ከተገደለ በኋላ ማለት ነው፡፡

"ሄሮድስ ግን ሰምቶ። እኔ ራሱን ያስቈረጥሁት ዮሐንስ ይህ ነው እርሱ ከሙታን ተነሥቶአል አለ። " (የማርቆስ ወንጌል 6: 16)

በተመሳሳይ ማቴወስ ላይም ይህንን እናገኛለን፡፡

በዚያ ዘመን የአራተኛው ክፍል ገዥ ሄሮድስ የኢየሱስን ዝና ሰማ፥ ለሎሌዎቹም። ይህ መጥምቁ ዮሐንስ ነው፤ እርሱ ከሙታን ተነሥቶአል፥ ስለዚህም ኃይል በእርሱ ይደረጋል አለ። የማቴዎስ ወንጌል 14፥1-2

ጥያቄው፡- ሄሮድስ እየሱስ በልጅነቱ ሳለ ነበር የሞተው ወይንስ በሰበካ ህይወቱም ወቅት ነበር?

99. እየሱስ በውሀ ላይ በሚራመድበት ወቅት ደቀመዛሙርት ምንድን ነበር የመለሱት?

"በታንኳይቱም የነበሩት። በእውነት **የእግዚአብሔር ልጅ ነህ** ብለው ሰገዱለት። " (የማቴዎስ ወንጌል 14: 33)

በዚህ አንቀጽ እንደምንመለከተው ተዐምራቱን ባዩ ጊዜ የእግዚአብሄር ልጅ ነህ ብለው እንደሰገዱለት ነው፡፡ በሌላ ቦታ ደግሞ እንዲህ የሚል እናገኛለን።

እነርሱ ግን በባሕር ላይ ሲሄድ ባዩት ጊዜ ምትሀት መሰላቸውና ጮኹ፥ ሁሉ አይተውታልና፥ ታወኩም። ወዲያውም ተናገራቸውና። አይዞአችሁ፤ እኔ ነኝ፥ አትፍሩ አላቸው። ወደ እነርሱም ወደ ታንኳይቱ ገባ፥ ነፋሱም ተወ፤ በራሳቸውም ያለ መጠን እጅግ ተገረሙ፤ **ስለ እንጀራው አላስተዋሉምና፤ ነገር ግን ልባቸው ደንዝዞ ነበር።**

ማርቆስ 6፡49-52

በዚህ አንቀጽ ደግሞ አይደለም የእግዚአብሄር ልጅ ነህ ብለው ሊሰግዱለት ይቅርን ተግባሩ ራሱ ምትሀት መስሏቸው ደንዝዘው ነበር፡፡ ስለመስገዳቸውም ሆነ የእግዚአብሄር ልጅ ስለማለታቸው ምንም የተገለጸ ነገር የለም፡፡

ጥያቄው፡- እየሱስ ተዐምሩን በሚፈጽምበት ወቅት ከሰዎች ያገኘው ምላሽ ምንድን ነበር?

100. ለእግዚአብሄር ፍጥረቱ መልካም ነበር ወይንስ አልነበረም?

"እግዚአብሔርም ያደረገውን ሁሉ አየ፥ **እነሆም እጅግ መልካም ነበረ።** ማታም ሆነ ጥዋትም ሆነ፥ ስድስተኛ ቀን። (ኦሪት ዘፍጥረት ፡ 31)

በዚህ አንቀጽ በእግዚአብሄር እይታ ፍጥረታት መልካም አንደነበሩ ይገልጻል፡፡ ነገር ግን በሌላ ቦታ እንዲህ ይላል

"እግዚአብሔርም **ሰውን በምድር ላይ በመፍጠሩ ተጸጸተ፥** በልቡም አዘነ። " (ኦሪት ዘፍጥረት 6: 6)

በዚህ ቦታ ደግሞ እግዚአብሄር በፈጠረው ፍጥረት ሲያዝንና ሲጸጸት እናያለን፡፡

ጥያቄው፡- እግዚአብሄር በእሱ እይታ ፍጥረታቱ መልካም ነበሩ ወይንስ አልነበሩም ነው?

101. እግዚአብሄር ቤተ መቅደስ ውስጥ ስሙ ለዘላለም ይኖራልን ወይንስ አይኖርም?

"እግዚአብሔርም ለሰሎሞን በሌሊት ተገልጦ እንዲህ አለው። ጸሎትህን ሰምቻለሁ፥ ይህንም ስፍራ ለራሴ ለመሥዋዕት ቤት መርጫለሁ። ዝናብ እንዳይወርድ ሰማያቱን ብዘጋ፥ ወይም ምድሪቱን ይበላ ዘንድ አንበጣን ባዝዘው፥ ወይም በሕዝብ ላይ ቸነፈር ብሰድድ፥ በስሜ የተጠሩት ሕዝቤ ሰውነታቸውን አዋርደው ቢጸልዩ፥ ፊቴንም ቢፈግሉ፥ ከክፉ መንገዳቸውም ቢመለሱ፥ በሰማይ ሆኜ እሰማለሁ፥ ኃጢአታቸውንም ይቅር እላለሁ፥ ምድራቸውንም እፈውሳለሁ። አሁንም በዚህ ስፍራ ለሚጸለይ ጸሎት ዓይኖቼ ይገለጣሉ፥ ጆሮቼም ያደምጣሉ። አሁንም ስሜ **ለዘላለም በዚያ ይኖር ዘንድ ይህን ቤት መርጫለሁ ቀድሻለሁም፤** ዓይኖቼና ልቤም ዘወትር በዚያ ይሆናሉ።

መጽሀፈ ዜና መዋዕል ካልዕ 7፥11-16

በዚህ አንቀጽ እንደምንመለከተው **እግዚአብሄር በቤተ መቅደስ ውስጥ ለዘላለም ይኖራል።** ነገር ግን ከዚህ በተቃራኒው በሌላ ቦታ ላይ እንዲህ የሚል እናገኛለን።

"ነገር ግን ነቢዩ። ሰማይ ዙፋኔ ነው ምድርም የእግሬ መረገጫ ናት፤ **ለእኔ ምን ዓይነት ቤት ትሠራላችሁ? ይላል ጌታ፥ ወይስ የማርፍበት ስፍራ ምንድር ነው? ይህንስ ሁሉ እጄ የሠራችው አይደለምን? እንዳለ፥ ልዑል የሰው እጅ በሠራችው አይኖርም።** " (የሐዋርያት ሥራ 7: 48-50)

በዚህ አንቀጽ ደግሞ እንደምናየው እግዚአብሄር ምንም አይነት የተሰራ ነገር ውስጥ አይኖርም ይላል።

ጥያቄው፡- እግዚአብሄር ቤተ መቅደስ ውስጥ ይኖራልን ወይንስ አይኖርም?

102. እግዚአብሄር ቁጣው ዘላለማዊ ነው ወይንስ ጊዜያዊ?

"ሂድና ይህን ቃል ወደ ሰሜን ተናገር፥ እንዲህም በል። ከዳተናይቱ እስራኤል ሆይ፥ ተመለሽ፥ ይላል እግዚአብሔር፤ መሐሪ ነኝና፥ **ለዘላለምም አልቈጣምና** በእናንተ ላይ ፊቴን አላደርግም፥ ይላል እግዚአብሔር። " (ትንቢተ ኤርምያስ 3: 12)

በዚህ አንቀጽ እግዚአብሄር ለዘላለም እንደማይቆጣ ይገልጻል። ነገር ግን በሌላ ቦታ ደግሞ መልሶ እንዲህ ይላል

"አንተም የሰጠሁህን ርስት ትለቅቃለህ **ለዘላለምም በማታውቃትም ምድር ለጠላቶቻችሁ ባሪያ አደርግሃለሁ፤**

ለዘላለም የሚነድደውን እሳት በቀኣጣዬ አንድዳችኋልና። " (ትንቢተ ኤርምያስ 17: 4)

በዚህ አንቀጽ ደግሞ የእግዚአብሄር የቁጣ እሳት ዘላለም እንደሚነድ ይገልጻል።

ጥያቄው፡- እግዚአብሄር ቁጣው ዘላለማዊ ነው ወይንስ አይደለም?

103. በእውኑ ምንም ጻድቅ የለምን ወይንስ አለ?

በመጽሀፍ ቅዱስ ውስጥ ብዙ ሰዎች ጻድቅ ተብለዋል። ለአብነትም

"እግዚአብሔርም **ኖኅን** አለው። አንተ ቤተሰቦችህን ሁሉ ይዘህ ወደ መርከብ ግባ፤ በዚህ ትውልድ በፊቴ ጻድቅ ሆነህ አይቼሃለሁና። " (አሪት ዘፍጥረት 7: 1)

በዚህ አንቀጽ ኖህ ጻድቅ እንደሆነ ይገልጻል።

"እግዚአብሔርም ሰይጣንን። በውኑ **ባሪያዬን ኢዮብን** ተመለከትኸውን? በምድር ላይ እንደ እርሱ ፍጹምና ቅን፥ እግዚአብሔርንም የሚፈራ፥ ከክፉትም የራቀ ሰው የለም፤ በከንቱም አጠፋው ዘንድ አንተ በእርሱ ላይ ምንም ብታንቀሳቅሰኝ፥ እስከ አሁን ፍጹምነቱን ይዞአል። " (መጽሐፈ ኢዮብ 2: 3)

በዚህ አንቀጽ ደግሞ ኢዮብ ፍጹምና ቅን ሰው እንደሆነ ተገልጽዋል።

"ሁለቱም በጌታ ትእዛዝና ሕግጋት ሁሉ ያለ ነቀፋ እየሄዱ **በእግዚአብሔር ፊት ጻድቃን ነበሩ።**

(የሉቃስ ወንጌል ፡ 6)

በዚህ አንቀጽ ደግሞ ዘካሪያስና ሚስቱ ጻድቅ ሲባሉ እናያለን።

ተመሳሳይም የተለያዩ ሰዎች ጻድቃን ተብለዋል፤ ለአብነት

ነኛ ዮሀንስ 3፡7 እንዲሁም የያዕቆብ 5፡16 መጥቀስ ይቻላል

ነገር ግን በተቃራኒው ሌላ ቦታ እንዲህ ሲል ጳውሎስ ይናገራል

"ጻድቅ የለም አንድ ስንኳ፤ አስተዋይም የለም፤ እግዚአብሔርንም የሚፈልግ የለም፤ ሁሉ ተሳስተዋል፥ " (ወደ ሮሜ ሰዎች 3: ፲፩)

ጥያቄው፡- ጻድቅ አለ ወይንስ የለም?

104. እግዚአብሄር ይታያል ወይንስ አይታይም?

"ያዕቆብም። **እግዚአብሔርን ፊት ለፊት አየሁ፥** ሰውነቴም ድና ቀረች ሲል የዚያን ቦታ ስም ጵኒኤል ብሎ ጠራው። " (ኦሪት ዘፍጥረት 32: 30)

በዚህ አንቀጽ እንደተገለጸው እግዚአብሄር ይታያል ነገር ግን በሌላ በብዙ ቦታዎች ላይ እግዚአብሄር እንደማይታይ ተገልጾ እናገኛለን።

ለአብነትም ዮሀንስ 1፡18 መመልከት ይቻላል፡፡

«መቼም ቢሆን **እግዚአብሔርን ያየው አንድ ሰንኳ የለም**፤ በአባቱ እቅፍ ያለ አንድ ልጁ እርሱ ተረከው።» ዮሀ 1፡18

ጥያቄው፡- እውን እግዚአብሄር ይታያል ወይንስ አይታይም?

105. ከእርግዝና በፊት ነው ወይንስ በኋላ?

"በስድስተኛውም ወር መልአኩ ገብርኤል ናዝሬት ወደምትባል ወደ ገሊላ ከተማ፥ ከዳዊት ወገን ለሆነው ዮሴፍ ለሚባል ሰው ወደ ታጨች ወደ አንዲት ድንግል ከእግዚአብሔር ዘንድ ተላከ፥ የድንግሊቱም ስም ማርያም ነበረ። መልአኩም ወደ እርስዋ ገብቶ። ደስ ይበልሽ፥ ጸጋ የሞላብሽ ሆይ፥ ጌታ ከአንቺ ጋር ነው፤ አንቺ ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ አላት። እርስዋም ባየችው ጊዜ ከንግግሩ በጣም ደነገጠችና። ይህ እንዴት ያለ ሰላምታ ነው? ብላ አሰበች። መልአኩም እንዲህ አላት። ማርያም ሆይ፥ በእግዚአብሔር ፊት ጸጋ አግኝተሻልና አትፍሪ። እነሆም፥ ትፀንሻለሽ ወንድ ልጅም ትወልጃለሽ፥ ስሙንም ኢየሱስ ትዪዋለሽ።" ሉቃስ 1፡26-31

በዚህ አንቀጽ በግልጽ እንደምንመለከተው የመላዕኩ ብስራት ማርያም ከመጸነሷ በፊት የመጣ ነው። ነገር ግን በሌላ ቦታ እንዲህ ይላል፦

"የኢየሱስ ክርስቶስም ልደት እንዲህ ነበረ። እናቱ ማርያም ለዮሴፍ በታጨች ጊዜ ሳይገናኙ ከመንፈስ ቅዱስ ፀንሳ ተገኘች። እጮኛዋ ዮሴፍም ጻድቅ ሆኖ ሊገልጣት ስላልወደደ በስውር ሊተዋት አሰበ። እርሱ ግን ይህን ሲያስብ፥ እነሆ የጌታ መልአክ በሕልም ታየው፥ እንዲህም አለ። የዳዊት ልጅ ዮሴፍ ሆይ፥ ከእርስዋ የተፀነሰው ከመንፈስ ቅዱስ ነውና እጮኛህን ማርያምን ለመውሰድ አትፍራ። ልጅም ትወልዳለች፤ እርሱ ሕዝቡን ከኃጢአታቸው ያድናቸዋልና ስሙን ኢየሱስ ትለዋለህ። " ማቴዎስ 1፡18-21

በዚህ አንቀጽ ደግሞ መላዕኩ ከመንፈስ ቅዱስ አንደምትወልድ ብስራት የተናገረው ከጸነሰች በኋላ ነው።

ጥያቄው፦ የመላዕኩ ተዐምራዊ ውልደት ብስራት የመጣው ከእርግዝና በፊት ነው ወይንስ በኋላ?

106. መላእኩ ብስራቱን የተናገረውስ ለማን ነበር?

"በስድስተኛውም ወር መልአኩ ገብርኤል ናዝሬት ወደምትባል ወደ ገሊላ ከተማ፥ ከዳዊት ወገን ለሆነው ዮሴፍ ለሚባል ሰው ወደ ታጨች ወደ አንዲት ድንግል ከእግዚአብሔር ዘንድ ተላከ፥ የድንግሊቱም ስም ማርያም ነበረ። መልአኩም ወደ እርስዋ ገብቶ። ደስ ይበልሽ፥ ጸጋ የሞላብሽ ሆይ፥ ጌታ ከአንቺ ጋር ነው፤ አንቺ ከሴቶች መካከል

የተባረክሽ ነሽ አላት። እርስዋም ባየችው ጊዜ ከንግግሩ በጣም ደነገጠችና። ይህ እንዴት ያለ ሰላምታ ነው? ብላ አሰበች። መልአኩም እንዲህ አላት። ማርያም ሆይ፥ በእግዚአብሔር ፊት ጸጋ አግኝተሻልና አትፍሪ። እነሆም፥ ትፀንሻለሽ ወንድ ልጅም ትወልጃለሽ፥ ስሙንም ኢየሱስ ትዪዋለሽ።" ሉቃስ 1፡26-31

በዚህ አንቀጽ በግልጽ እንደምንመለከተው መላዕኩ በቀጥታ ያናግራት የነበረው እራሷ ማርያምን ነው፡፡ ነገር ግን በሌላ ቦታ እንዲህ ይላል፡-

"የኢየሱስ ክርስቶስም ልደት እንዲህ ነበረ። እናቱ ማርያም ለዮሴፍ በታጨች ጊዜ ሳይገናኙ ከመንፈስ ቅዱስ ፀንሳ ተገኘች። እጮኛዋ ዮሴፍም ጻድቅ ሆኖ ሊገልጣት ስላልወደደ በስውር ሊተዋት አሰበ። እርሱ ግን ይህን ሲያስብ፥ እነሆ የጌታ መልአክ በሕልም ታየው፥ እንዲህም አለ። የዳዊት ልጅ ዮሴፍ ሆይ፥ ከእርስዋ የተፀነሰው ከመንፈስ ቅዱስ ነውና እጮኛህን ማርያምን ለመውሰድ አትፍራ። ልጅም ትወልዳለች፤ እርሱ ሕዝቡን ከኃጢአታቸው ያድናቸዋልና ስሙን ኢየሱስ ትለዋለህ። " ማቴወስ 1፡18-21

በዚህ አንቀጽ ደግሞ መላዕኩ ያናገረው ዮሴፍን እንደነበር ተገልጿዋል፡፡

ጥያቄው፡- መላዕኩ ስለተዐምራዊው ውልደት ያናገረው ማንን ነበር? የሚል ነው

107. ከተወለደ በኋላስ ስሙ ማን ይባላል?

"እነሆ፥ ድንግል ትፀንሳለች ልጅም ትወልዳለች፥ **ስሙንም አማኑኤል** ይሉታል የተባለው ይፈጸም ዘንድ ይህ

ሁሉ ሆኖአል፥ ትርጓሜውም። እግዚአብሔር ከእኛ ጋር የሚል ነው። " (የማቴዎስ ወንጌል ፡ 23)

በዚህ አንቀጽ ስያሜው **አማኑኤል** ተብሎ እንደሚጠራ ይገልጻል። ነገር ግን ትንሽ ወረድ ብሎ እንዲህ ይለናል

"የበኩር ልጅዋንም እስክትወልድ ድረስ አላወቃትም፤ **ስሙንም ኢየሱስ አለው።** (የማቴዎስ ወንጌል ፡ 25)

በዚህ አንቀጽ ደግሞ እየሱስ እንደተባለ ይገልጻል። አማኑኤል የሚለው ቃል እየሱስ ወንጌል ውስጥ የትም ቦታ ሲጠራበት አንመለከትም።

ጥያቄው፡- ታዲያ የቱ ነው ትክክል?

108. ከሰማይ የመጣው ድምጽ የተናገረው ለእየሱስ ነበር ወይንስ ለተሰበሰበው ህዘብ?

"ወዲያውም ከውኃው በወጣ ጊዜ ሰማያት ሲቀደዱ መንፈስም እንደ ርግብ ሲወርድበት አየና። **የምወድህ ልጄ አንተ ነህ፥ በአንተ ደስ ይለኛል** የሚል ድምፅ ከሰማያት መጣ።" ማርቆስ ፡10-11

በዚህ አንቀጽ የሚነግረን ድምጹ ቀጥታ ሲያናግረው የነበረው እየሱስን ነበር። ምክንያቱም ይጠቀመው የነበረው ቃል «የምወድህ» «አንተ ነህ» ወዘተ እያለ ነበር።

ነገር ግን በሌላ ቦታ

"ኢየሱስም ከተጠመቀ በኋላ ወዲያው ከውኃ ወጣ፤ እነሆም፥ ሰማያት ተከፈቱ የእግዚአብሔርም መንፈስ እንደ ርግብ ሲወርድ በእርሱ ላይም ሲመጣ አየ፤ እነሆም፥ ድምፅ ከሰማያት መጥቶ። **በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው** አለ።" ማቴወስ 3፡16-17

በዚህ አንቀጽ ደግሞ የሚነግረን ድምጹ ይናገር የነበረው አንተ እያለ ሳይሆን እርሱ እያለ በሶስተኛ መደብ አድረጎ ለተሰበሰበው ህዝብ ነበር።።

ጥያቄው፡- ድምጹ የተናገረው ቀጥታ ለእየሱስ ነበር ወይንስ ለተሰበሰበው ሰው?

109. እየሱስ ወደ ቅፍርንሆም የሄደው ብቻውን ነው ወይንስ ከደቀመዛሙርቱ ጋር

"ወደ ገሊላ ከተማም ወደ ቅፍርናሆም ወረደ። በሰንበትም ያስተምራቸው ነበር፤ " (የሉቃስ ወንጌል 4፡ 31)

በዚህ አንቀጽ ስንመለከት ወደ ቅፍርናሆም ደቀመዛሙርት አብረውት እንደወረዱ የሚገልጽ ምንም ነገር የለውም አንቀጹም "ወረደ" ሲል በነጠላ ነው የሚገልጸው።።

ነገር ግን ሌላ ቦታ

"ወዲያውም ጠራቸው አባታቸውንም ዘብዴዎስን ከሞያተኞቹ ጋር በታንኳ ላይ ትተው ተከትለውት ሄዱ። ወደ ቅፍርናሆምም ገቡ፤ ወዲያውም በሰንበት ወደ ምኵራብ ገብቶ አስተማረ። " ማርቆስ 1፡20-21

በዚህ አንቀጽ ደግሞ የምናየው እየሱስ ወደ ቅፍርናሆም የሄደው ከደቀመዛሙርቱ ጋር እንደሆነ ነው፡፡

ጥያቄው፡- ታዲያ የቱ ነው ትክክለኛ ዘገባ?

110. ጴጥሮስ ወንጌልን የሰበከው ለአይሁዳውያን ብቻ ነው ወይንስ ለአህዛብም ጭምር?

"እነዚህን አሥራ ሁለቱን ኢየሱስ ላካቸው፥ አዘዛቸውም፥ እንዲህም አለ። **በአሕዛብ መንገድ አትሂዱ፥** ወደ ሳምራውያንም ከተማ አትግቡ፤ " (የማቴዎስ ወንጌል 10: 5)

በዚህ አንቀጽ መሰረት እየሱስ ጴጥሮስን ጨምሮ አስራ ሁለቱንም ደቀመዛሙርት ወደ ጠፉት በጎች ወደ እስራኤላውያን (ማቴወስ 10፡6) እንጂ ወደ አህዛብ እንዳይሄዱ አዟቸዋል፡፡

በተመሳሳይ ጳውሎስ ሲናገር

«ተመልሰው ግን ጴጥሮስ ለተገረዙት የሆነው ወንጌል አደራ እንደ ተሰጠው እንዲሁ ለእኔ ላልተገረዙት የሆነው ወንጌል አደራ እንደ ተሰጠኝ እዩ፤ ለተገረዙት ሐዋርያ እንዲሆን ለጴጥሮስ የሠራለት፥ ለእኔ ደግሞ ለአሕዛብ ሐዋርያ እንድሆን ሠርቶአልና።" ገላትያ 2፡7-8

የተገረዙት የተባሉት አይሁዳውያን ሲሆኑ ጴጥሮስ ለአህዛብ ሳይሆን ለነኝህ የሆነው ወንጌል እንደተሰጠው ጳውሎስ በገላትያ መልዕክቱ ይናገራል፡፡ በተመሳሳይ እንደ

ጳውሎስ አገላለጽ ጳውሎስ ላልተገረዙት ማለትም ለሮማውያን የሆነው ወንጌል እንደተሰጠው ይናገራል።

ነገር ግን በሌላ ቦታ

"ከብዙ ክርክርም በኋላ ጴጥሮስ ተነሥቶ እንዲህ አላቸው ወንድሞች ሆይ፥ አሕዛብ ከአፌ የወንጌልን ቃል ሰምተው ያምኑ ዘንድ እግዚአብሔር በመጀመሪያው ዘመን ከእናንተ እኔን እንደ መረጠኝ እናንተ ታውቃላችሁ። " (የሐዋርያት ሥራ 15: 7)

በዚህ አንቀጽ ደግሞ እራሱ ጴጥሮስ እኔ አህዛብንም እንድሰብክ ተመርጫለሁ ሲል እናያለን።

ጥያቄው፡- ጴጥሮስ ለአህዛብ ወንጌል እንዲሰብክ ተመርጧል ወይንስ አልተመረጠም?

III. እየሱስ የጴጥሮስን አማት የፈወሳት ለምጻሙን ከፈወሰ በኋላ ነው ወይንስ በፊት?

"ኢየሱስም ለመቶ አለቃ። ሂድና እንዳመንህ ይሁንልህ አለው። ብላቴናውም በዚያች ሰዓት ተፈወሰ። ኢየሱስም ወደ ጴጥሮስ ቤት ገብቶ አማቱን በንዳድ ታማ ተኝታ አያት፤ እጅዋንም ዳሰሰ፥ ንዳዱም ለቀቃት፤ ተነሥታም አገለገለቻቸው።" ማቴወስ 8፡13-15

በዚህ አንቀጽ ስንመለከት እየሱስ ለምጻሙን ከፈወሰ በኋላ (ሙሉውን ታሪኩን ማቴወስ 8፡1 ጀምሮ ማየት ይቻላል) ወደ ጴጥሮስ አማት በመግባት እንደፈወሳት ነው ።

ነገር ግን በሌላ ቦታ

የስምዖንም አማት በንዳድ ታማ ተኝታ ነበር፥ ስለ እርስዋም ወዲያው ነገሩት። ቀርቦም እጅዋን ይዞ አስነሣት ንዳዱም ወዲያው ለቀቃትና አገለገለቻቸው።" ማርቆስ 1፡30-31

ሙሉ ታሪኩ እስከ 41 ድረስ መመልከት ይቻላል። ተጨማሪም ሉቃስ 4፡38 እስከ ሉቃስ 5፡13 ያገኙታል

በዚህ አንቀጽ ደግሞ የሚነግረን ደግሞ እየሱስ ለምጻሙን ከመፈወሱ በፊት የጴጥሮስን አማት አንደፈወሳትና ከዚያ በኋላ ለምጻሙን አንደፈወሰው ነው።

ጥያቄው፡- እየሱስ የጴጥሮስን አማት የፈወሳት ለምጻሙን ከፈወሰ በኋላ ነው ወይንስ በፊት

112. እየሱስ ወላጅን ስለማክበር

"ትእዛዛትን ታውቃለህ፤ አታመንዝር፥ አትግደል፥ አትስረቅ፥ በሐሰት አትመስክር፥ አታታልል፥ አባትህንና እናትህን አክብር አለው። " (የማርቆስ ወንጌል 10: 19)

በተመሳሳይ ሉቃስ 18፡20 ማቴወስ 19፡19 ማርቆስ 7፡10 ተመሳሳይ መልዕክቶችን ይዘዋል

በነዚህ አንቀጽ እየሱስ እንደሚነግረን ወላጆቻችንን ልናከብር እንደሚገባ ነው። እሱም ከመጣበት ተልዕኮ አንዱ ይህንን ትእዛዝ ሊያስከብር ነው።

ነግር ግን በሌላ ቦታ እንዲህ የሚል አንገኛለን

‹ዘበምድር ላይ ሰላምን ለማምጣት የመጣሁ አይምሰላችሁ፤ ሰይፍን እንጂ ሰላምን ለማምጣት አልመጣሁም። ሰውን ከአባቱ፥ ሴት ልጅንም ከእናትዋ፥ ምራትንም ከአማትዋ እለያይ ዘንድ መጥቻለሁና፤ " ማቴወስ 10:34-35

ተጨማሪ ሉቃስ 12፡51-53 እንዲሁም ሉቃስ 14፡26 መመልከት ይቻላል

በዚህ አንቀጽ ደግሞ እየሱስ የመጣሁት እናንተን ልለያይ ነው ይለናል፡፡ ወላጅና ልጅ ከተለያየ ምኑን ይከባበራል?

ጥያቄው፡- የእየሱስ ትምህርት ወላጅና ልጅ የሚያከባብር ወይንስ የሚለያይ ነው?

113. እየሱስና «ሰድብ»

"እኔ ግን እላችኋለሁ፥ በወንድሙ ላይ የሚቆጣ ሁሉ ፍርድ ይገባዋል፤ ወንድሙንም ጨርቃም የሚለው ሁሉ የሸንጎ ፍርድ ይገባዋል፤ ደንቆሮ የሚለውም ሁሉ የገሃነመ እሳት ፍርድ ይገባዋል። " (የማቴዎስ ወንጌል 5: 22)

በዚህ አንቀጽ እየሱስ እንደሚነግረን ደንቆሮ ብሎ የሚሳደብ የገሀነብ ፍርድ ይገባዋል፡፡

በሌላ ቦታ ግን እራሱ እየሱስ ይህንን ስድብ ሲጠቀም እንመለከታለን፡፡

"እናንተ ደንቆሮዎችና ዕውሮች፥ ማናቸው ይበልጣል? ወርቁ ነውን? ወይስ ወርቁን የቀደሰው ቤተ መቅደስ? " (የማቴዎስ ወንጌል 23: 17)

ተጨማሪ

"እናንት ደንቆሮዎች፥ የውጭውን የፈጠረ የውስጡን ደግሞ አልፈጠረምን? " (የሉቃስ ወንጌል ፲፡ 40)

ጥያቄው፡- እየሱስ ከራሱ ንግግር ጋር እንዴት ይጋጫል? ደግሞስ በእየሱስ አገላለጽ መሰረት አላህ ይጠብቀንና እየሱስ የገሀነብ ፍርድ ይገባዋል ልንል ነው?

፲14. መልካም ስራ በሰው ፊት ነው ወይንስ በድብቅ ነው መሆን ያለበት?

"ለሰዎች ትታዩ ዘንድ ምጽዋታችሁን በፊታቸው እንዳታደርጉ ተጠንቀቁ፤ ያለዚያ በሰማያት ባለው አባታችሁ ዘንድ ዋጋ የላችሁም። እንግዲህ ምጽዋት ስታደርግ፥ ግብዞች በሰው ዘንድ ሊከበሩ በምኩራብ በመንገድም እንደሚያደርጉ በፊትህ መለከት አታስነፋ፤ እውነት እላችኋለሁ፥ ዋጋቸውን ተቀብለዋል። አንተ ግን ምጽዋት ስታደርግ ምጽዋትህ በስውር እንዲሆን ቀኝህ የምትሠራውን ግራህ አትወቅ፤ በስውር የሚያይ አባትህም በግልጥ ይከፍልሃል። ማቴወስ 6፡1-4

በዚህ አንቀጽ መሠረት እየሱስ እንደሚነግረን መልካም ስራ በስውር መሆን እንዳለበት ነው፡፡ ነገር ግን በሌላ ቦታ እንዲህ ይላል

"መልካሙን ሥራችሁን አይተው በሰማያት ያለውን አባታችሁን እንዲያከብሩ ብርሃናችሁ እንዲሁ በሰው ፊት ይብራ። " (የማቴዎስ ወንጌል 5: 16)

ጥያቄው፦ መልካም ስራ በሰው ፊት ነው ወይንስ በድብቅ ነው መሆን ያለበት?

115. ሴት ልጅ መውለድ መባረክ ነው ወይንስ መርከሰ?

"እግዚአብሔርም ባረካቸው፥ እንዲህም አላቸው። ብዙ፥ ተባዙ፥ ምድርንም ሙሉአት፥ ግዙአትም፤ የባሕርን ዓሦችና የሰማይን ወፎች በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትንም ሁሉ ግዙአቸው። " (ኦሪት ዘፍጥረት 1: 28)

በዚህ አንቀጽ እንደምንመለከተው እግዚአብሄር ሁለቱንም (አዳምና ሄዋን) ብዙ ተባዙ ሲል እንደባረካቸው ነው። ነገር ግን በሌላ ቦታ መልሶ እንዲህ ሲል እንመለከታለን

"እግዚአብሔርም ሙሴን እንዲህ ብሎ ተናገረው። ለእስራኤል ልጆች እንዲህ ብለህ ንገራቸው። ሴት ብታረግዝ ወንድ ልጅም ብትወልድ፥ ሰባት ቀን ያህል የረከሰች ናት፤ እንደ ሕመምዋ መርገም ወራት ትረክሳለች። በስምንተኛውም ቀን ልጁ ከሥጋው ሸለፈት ይገረዝ። ከደምዋም እስክትነጻ ሠላሳ ሦስት ቀን ትቀመጥ፤ የመንጻትዋ ቀንም እስኪፈጸም ድረስ የተቀደሰን ነገር አትንካ፥ ወደ መቅደስም አትግባ። ሴት ልጅም ብትወልድ እንደ መርገምዋ ወራት ሁለት ሳምንት ያህል የረከሰች ናት፤ ከደምዋም እስክትነጻ ድረስ ስድሳ ስድስት ቀን ትቀመጥ። የመንጻትዋ ወራትም በተፈጸመ ጊዜ፥ ለወንድ ልጅ

ወይም ለሴት ልጅ፥ የአንድ ዓመት ጠቦት ለሚቃጠል መሥዋዕት፥ የርግብም ግልገል ወይም ዋኖስ ለኃጢአት መሥዋዕት ወደ መገናኛው ድንኳን ደጃፍ ወደ ካህኑ ታምጣለት። እርሱም በእግዚአብሔር ፊት ያቀርበዋል ያስተሰርይላትማል፤ ከደምዋም ፈሳሽ ትነጻለች። ወንድ ወይም ሴት ለምትወልድ ሴት ሕጉ ይህ ነው። ጠቦት ለማምጣት ገንዘብዋ ያልበቃት እንደ ሆነ ሁለት ዋኖሶች ወይም ሁለት የርግብ ግልገሎች፥ አንዱን ለሚቃጠል መሥዋዕት ሌላውንም ለኃጢአት መሥዋዕት ታቀርባለች፤ ካህኑም ያስተሰርይላታል፥ እርስዋም ትነጻለች።" ኦሪት ዘሌዋውያን 12፡1-8

ጥያቄው፡- የሴት ልጅ የወሊድ ሂደት መባረክ ነው ወይንስ መርከስ?

116. ቃየል ከእግዚአብሄር ፊት ተሰውሯልን?

«እኔ የቅርብ አምላክ ነኝ እንጂ የሩቅ አምላክ አይደለሁም። ሰው በስውር ቢሸሸግ፥ እኔ አላየውምን? ሰማይንና ምድርንስ የሞላሁ እኔ አይደለሁምን? ይላል እግዚአብሔር፡፡ ትንቢተ ኤርሚያስ 23፡23-24

በዚህ አንቀጽ እንደምንመለከተው ከእግዚአብሄር ፊት ወጥቶ ማንም እንደማይሸሸግ ነው፡፡ ነገር ግን ሌላ ቦታ ላይ እንዲህ የሚል ቃል እናገኛለን

«ቃየንም ከእግዚአብሔር ፊት ወጣ፤ ከዔድንም ወደ ምሥራቅ በኖድ ምድር ተቀመጠ።» ኦሪት ዘፍጥረተ 4፡16

ጥያቄው፡- ቃየል ከእግዚአብሄር ፊት ወጥቷል ወይንስ አልወጣም?

117. የአብርሀም አባት ታራም አብርሀምን ሲወልድ እድሜው ስንት ነበር?

«ታራም መቶ ዓመት ኖረ፥ አብራምንና ናኮርን ሐራንንም ወለደ።» ኦሪት ዘፍጥረት 11፡16

በዚህ አንቀጽ አንደምንመለከተው የአብርሀም አባት ታራም አብርሀምን ሲወልድ እድሜው መቶ እንደሆነ ነው፡፡ ነገር ግን በሌላ ቦታ ስንመለከት እንዲህ የሚል ቃል እናገኛለን

« የታራም ዕድሜ ሁለት መቶ አምስት ዓመት ሆነ፤ ታራም በካራን ሞተ።» ኦሪት ዘፍጥረት 11፡32

በዚህ አንቀጽ መሰረት ታራም ሲሞት አብርሀም እድሜው 105 እንደሆነ እንረዳለን። ምክንያቱም አብርሀምን በ100 አመቱ ከወለደውና እርሱ በ205 አመቱ ከሞተ፤ 205-100 = 105 ስለሚሆን ማለት ነው። ነገር ግን ትንሽ እልፍ ብሎ ታራም ከሞተ በኋላ የእብርሀምን እድሜ ሲነግረን እንዲህ ይላል፡፡

«አብራምም እግዚአብሔር እንደ ነገረው ሄደ፤ ሎጥም ከእርሱ ጋር ሄደ፤ አብራምም ከካራን በወጣ ጊዜ የሰባ አምስት ዓመት ሰው ነበረ።»

በዚህኛው አንቀጽ ደግሞ ጭራሽ የአብርሀም እድሜ ተቀንሶ 75 እንደሆነ ይነግረናል፡፡

ጥያቄው፡- ታዲያ የቱ ነው ትክክል?

118. ከባቢሎን ግንብ ግንባታ በፊት ብዙ ቋንቋዎች ነበሩ ወይንስ አልነበሩም?

«ከእነዚህም የአሕዛብ ደሴቶች ሁሉ በየምድራቸው በየቋንቋቸው በየነገዳቸው በየሕዝባቸው ተከፋፈሉ።»

ኦሪት ዘፍጥረት 10፡5

በዚህ አንቀጽ መሰረት በወቅቱ ከባቢሎን ግንባታ በፊት ብዙ ቋንቋዎች እንደነበሩ እንረዳለን፡፡ ነገር ግን መልሶ እዛው መጽሀፍ አንድ ምዕራፍ ከፍ ብሎ ተቃራኒ ነገር ይነግረናል

«ምድርም ሁሉ በአንድ ቋንቋና በአንድ ንግግር ነበረች።»
ኦሪት ዘፍጥረት 11፡1

በዚህ አንቀጽ ደግሞ ግንባታው ከመጀመሩ በፊት የነበረው ቋንቋ አንድ ብቻ ነበር ይላል፡፡

ጥያቄው፡- ከባቢሎን ግንብ ግንባታ በፊት ብዙ ቋንቋዎች ነበሩ ወይንስ አልነበሩም?

119. እግዚአብሄር ስለ መስዋዕት አዟል ወይንስ አላዘዘም?

«እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ ለሌላ መሥዋዕታችሁ የሚቃጠለውን መሥዋዕታችሁን ጨምሩ፥ ሥጋውንም ብሉ። ከግብጽ ምድር ባወጣኋችሁ ቀን ስለሚቃጠል መሥዋዕትና ስለ ሌላ **መሥዋዕት ለአባቶቻችሁ አልተናገርሁምና፥ አላዘዝኋቸውምም።**» ኤርሚያስ 7፡21-22

በዚህ ጥቅስ መሰረት እግዚአብሄር ለአባቶቻቸው መስዋዕት አላዘዘም፣ አልተናገረምም!! ነገር ግን በሌላ የተለያዩ ቦታዎች ላይ እራሱ እግዚአብሄር ስለመስዋዕት ዝርዝር ትእዛዞችን ሲሰጥ እንመለከታለን፡፡

«የጭቃ መሠዊያ ሥራልኝ፥ የሚቃጠለውንና የደኅንነት መሥዋዕትህን በጎችህንም በሬዎችህንም ሠዋበት፤ **ስሜን በማሳስብበት ስፍራ ሁሉ ወደ አንተ መጥቼ እባርክሃለሁ።**» ኦሪት ዘጸአት 20፡24

በዚህ ብቻ አያበቃም በሌሎች ተመሳሳይ ቦታዎችም ሀሳቡን ሲያጠናክር እንመለከታለን፡፡

ለምሳሌ ዘፍጥረት 15፡9

ዘጸአት 29፡10-42፣ ዘሌዋውያን 1፡1-7 ወዘተ...

ጥያቄው፡- ታዲያ እግዚአብሄር ስለ መስዋዕት አዟል ወይንስ አላዘዘም?